LAPSLEY / BROOKS FOUNDATION, INC.
1701 N. GREENVILLE AVE. ST. 810
RICHARDSON, TEXAS 75081, USA

# የዓለም ታሪክ

ከጂዎግራፊ ፡ ጋር ፡ የተያያዘ ።

ተ ተ ረ ጐ መ ፡
ከዮሐንስ ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፡ ዘብሔረ ፡ ተጕለት ፡
በ፲፱፻፴፮ ፡ ዓ. ም.

በትምህርትና ፡ በሥነ ፡ ጥበብ ፡ ሚኒስቴር ፡ ትጋት ፡ ታተመ ።

-- Ex Libris --
B. N. Lapsley
375 Willow Wood
Murphy, Texas 75094

ተጎትመ ፡ ዝንቱ ፡ መጽሐፍ ፡ በ፲ ፡ ወጀቱ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥቱ ፡
ለቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፤ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ።

አዲስ ፡ አበባ ፡ ፲፱፻፵ ፡ ዓ. ም.

በብርሃንና ፡ ሰላም ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ታተመ ፤ ፳፰ ፡ ፯ ፡ ፴፯ ፡ ቁ. [illegible] ፡ መ. ፳፭፻ ።



ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ።

## ምርመራ ።

ገጽ ።

ምዕራፍ ፡ ፻፷፰ በእስያ ፡ በአፍሪካ ፡ የመንግሥታት ፡ ጥንታዊነት ። . ፩፻፸፰
» ፻፷፱ የመንግሥታት ፡ ጸንቶ ፡ መኖር ፡ በኤውሮጳ ። . . ፩፻፹፩
» ፻፸ የአገሮች ፡ ጥንታዊ ፡ ስም ። . . . . . ፩፻፹፪
» ፻፸፩ የመንግሥት ፡ መሠረትና ፡ በዕውቀት ፡ ከፍ ፡ እያለ ፡ መሄድ ። ፩፻፹፱
» ፻፸፪ የቤት ፡ ሥራ ፡ ዕውቀት ፡ ግብርና ፡ ያትክልት ፡ ሥራ ። ፩፻፺፬
» ፻፸፫ ንግድ ። . . . . . . . ፩፻፺፭
» ፻፸፬ ሥዕል ፡ መሣል ፡ ድንጊያ ፡ መጥረብ ፡ ሙዚቃ ። . ፩፻፺፮
» ፻፸፭ መጀመርያ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ብልሀት ፡ እንዴት ፡ እየተገለጠ ፡
እንደመጣ ። . . . . . . . ፩፻፺፯
» ፻፸፮ ጥበባት ፡ የተገኙበትና ፡ የተገለጡበት ፡ ዘመን ። ፩፻፺፱

# የዓለም ፡ ታሪክ ።

## ምዕራፍ ፡ ፩ ፡ መግቢያ ።

### በባሉን ፡ ተቀምጦ ፡ በሰ ፡ መሄድና ፡ በሰሚታየው ፡ አዲስ ፡ ነገር ።

በባሉን ፡ ተቀምጣችሁ ፡ በአየር ፡ ውስጥ ፡ እየዞራችሁ ፡ አገሩን ፡ ሁሉ ፡ ብትመለከቱ ፡ ስንት ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ነገር ፡ ባያችሁ ፡! ያን ፡ ጊዜውን ፡ ከተማውንና ፡ ወንዙን ፡ ተራራውንና ፡ ከረፍታውን ፣ ጕድጓዳውን ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ ቍልቍል ፡ እየተመለከታችሁ ፡ ለመሄድ ፡ ትችላላችሁ ።

፩ ፡ ጂዎግራፊ ፡ የሚሉትን ፡ ለመማር ፡ ይህ ፡ እንዴት ፡ መልካም ፡ በሆነ ፡ ? እንደምታውቁት ፣ ጂዎግራፊ ፡ ማለት ፡ መንገደኞች ፡ ሲሄዱ ፡ ሳሉ ፡ በየሄዱበት ፡ የሚገጥሟቸው ፡ የከተሞች ፣ የወንዞች ፣ የጕድጓዳው ፡ አገሮች ፣ የከረፍቶች ፣ የተራሮችና ፡ የሌሎችም ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ ሁኔታ ፡ ነው ።

፪ ፡ ከተሞች ፡ የተሠሩበትን ፣ ወንዞች ፡ የሚወርዱበትን ፣ ተራሮች ፡ ያሉበትን ፡ ስፍራ ፡ እንደ ፡ ሥዕል ፡ ሆኖ ፡ የሚታያችሁን ፡ በካርታ ፡ ከማየት ፡ ይልቅ ፡ ይህ ፡ እንዴት ፡ ደስ ፡ ያሰኝ ፡ ይመስላችኋል ፡! ነገር ፡ ግን ፡ በአየር ፡ አድርገን ፡ በባሉን ፡ የምንሄድ ፡ ሰዎች ፣ እጅግ ፡ ጥቂቶች ፡ ስለሆንን ፡ የሚቻለንን ፡ ያህል ፡ የጂዎግራፊን ፡ ትምህርት ፡ በካርታ ፡ ብንማር ፡ ይበቃናል ።

፫ ፡ ወደ ፡ ሩቅ ፡ አገር ፡ ሄደን ፡ ከቶ ፡ ካሁን ፡ ቀድም ፡ አይተነው ፡ የማናውቅ ፡ ማር ፡ የበቀለበት ፡ ልዩ ፡ የሆነ ፡ ከደንጊያ ፡ የተሠራ ፡ ሕንጻ ፣ ከተሠራም ፡ ፭፻ ፡ ዘመን ፡ እንደ ፡ ሆነው ፡ የሚያሳይ ፡ ምልክት ፡ ብናገኝ ።

፬ ፡ ወደዚህም ፡ አዳራሽ ፡ ውስጥ ፡ ገብተን ፡ እጅግ ፡ ሰፊ ፡ የሆኑ ፡ የጨለሙ ፡ ጓዳዎች ፡ ብናይ ፣ እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ እዚሁ ፡ አዳራሽ ፡ ውስጥ ፡ በገባን ፡ ጊዜ ፡ ከሞቱ ፡ ሁለት ፣ ወይም ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ የሆናቸውን ፡ ሰዎች ፡ መቃብርና ፡ ዐጽማቸው ፡ ካለበት ፡ በታች ፡ ስማቸው ፡ የተቀረጸበትን ፡ ደንጊያ ፡ ብናገኝ ፣

፭ ፡ ይህንንም ፡ ሁሉ ፡ ስናይ ፡ ምን ፡ እናስብ ፡ ይመስላችኋል ፡ ? ይህን ፡ ሕንጻ ፡ የሠራ ፡ ማን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፣ የተሠራውስ ፡ ምን ፡ ጊዜ ፣ ምክንያቱስ ፡ ለምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ስናስብ ፡ እንደ ፡ አዲስ ፡ ነገር ፣ ሆኖ ፡ አይገርመን ፡ ይሆን ፡ ? እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ የሚያስገርም ፡ ሕንጻ ፡ የሠሩትን ፡ ሕዝብ ፡ ዝና ፡ ለመስማት ፡ አንናፍቅምን ፡ ? ወደ ፡ ኋላችን ፡ ተመልሰን ፡ ከምዕት ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ የነበረውን ፡ የቀድሞ ፡ ታሪክ ፡ ለመማር ፡ አንመኝ ፡ ይሆን ፡ ?

፮ ፡ ይህ ፡ ታላቅ ፡ ሕንጻ ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ወይስ ፡ ለምን ፡ እንደ ፡ ተሠራ ፡ የሚነግረን ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ የኖረ ፡ አንድ ፡ ኰሳሳ ፡ ሽማግሌ ፡ ብናገኝ ፣ ባጠገቡ ፡ ተቀምጠን ፡ ለመስማት ፡ እንዴት ፡ በናፈቅን ፡ ነበር ። ፣ ይህንኑ ፡ ሕንጻ ፡ ስለ ፡ ሠሩት ፡ ሕዝብና ፡ በውስጡም ፡ ስለ ፡ ተቀበሩት ፡ ሰዎች ፡ እንዲተርክልን ፡ ስንት ፡ ሺህ ፡ ጥያቄ ፡ ባቀረብንለት ፡ ነበር ። ፣

፯ ፡ አሁን ፡ ወደማታውቁት ፡ አገር ፡ ብትሄዱ ፡ እንደዚሁ ፡ እንደ ፡ ነገርኋችሁ ፡ ያሉ ፡ አያሎች ፡ ሕንጻዎች ፡ ይገጥሙዋችኋል ። ከቶውንም ፡ ከተሠሩ ፡ ፱፻ ፡ ዘመን ፡ የሆናቸውን ፡ ታገኛላችሁ ።

፰ ፡ እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ ኢጣሊያና ፡ ወደ ፡ ግሪክ ፣ ወደ ፡ ግብፅም ፣ ወይም ፡ ወደ ፡ እስያ ፡ ጕዞዋችሁን ፡ ብትቀጥሉ ፡ የዛሬ ፡ ሁለት ፣ ወይም ፡ ሦስት ፡ ሺህ ፡ ዓመት ፡ የነበሩ ፡ የቤተ ፡ መቅደስና ፡ የቤተ ፡ መንግሥት ፣ ከጥንት ፡ ተሠርተው ፡ የነበሩ ፡ የከተሞች ፡ ፍራሾች ፡ ታገኛላችሁ ። ከነዚህም ፡ አያሌቹን ፡ በያችሁ ፡ ጊዜ ፡ በውበታቸውና ፡ በታላቅነታቸው ፡ ሳትገረሙ ፡ አትቀሩም ።

፱ ፡ በማታውቋቸው ፡ አገሮች ፡ ስትጓዙ ፡ እንደዚህ ፡ ያሉት ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ ይገጥሙዋችኋል ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ታሪካቸውን ፡ የሚነግራችሁ ፡ ሽማግሌ ፡ አታገኙምና ፡ እንዴት ፡ ታደርጋላችሁ ፡ ? እንግዲያስ ፡ ሁሉን ፡ ዞራችሁ ፡ አይታችሁ ፡ ከተመለሳችሁ ፡ በኋላ ፡ ይህን ፡ ታሪክ ፡ በማንበብ ፡ ያለፉትን ፡ ዘመናት ፡ ታሪክ ፡ ስትሰሙ ፡ ምናልባት ፡ ደስ ፡ ሳይላችሁ ፡ አይቀርም ።

፲ ፡ እንግዲህ ፡ ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ ከሚያነቡ ፡ ሰዎች ፡ አያሌቹ ፡ ዓለምን ፡ ሁሉ ፡ ለመዞር ፣ ወይም ፡ የሩቆችን ፡ አገሮች ፡ ታሪክ ፡ ለማንበብ ፡ ይፈልጉ ፡ ይሆናል ። ምናልባት ፡ ደግሞ ፡ ከጥንት ፡ ዘመን ፡ የነበረውን ፡ ታሪክ ፡ ሽማግሌ ፡ ሲነግራቸው ፡ እንደ ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ ሆኖ ፡ ይታያቸው ፡ ይሆናል ። አንባቢው ፡ ፈጽሞ ፡ ካልደከመ ፡ በቀር ፡ የምተርክለትን ፡ ተቀምጦ ፡ እንዲሰማኝ ፡ እለምነዋለሁ ።

## ጥያቄ ።

፩ ፡ ሰው ፡ በባሉን ፡ ተቀምጦ ፡ አገሩን ፡ ሁሉ ፡ ቢዞር ፡ ምን ፡ ያያል ፡ ?
፪ ፡ ጂዎግራፊ ፡ ምን ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ?
፫ ፡ ካርታ ፡ ምንድን ፡ ነው ፡ ?
፬ ፡ የቀድሞ ፡ ከተማዎችን ፡ ፍራሽ ፡ ስናገኝ ፡ ምን ፡ ለማወቅ ፡ እናስባለን ፡ ?
፭ ፡ ወደ ፡ ሩቅ ፡ አገር ፡ የሚሄድ ፡ መንገደኛ ፡ በሌላ ፡ አገር ፡ ከምን ፡ ጋር ፡ ይገናኛል ፡ ?
፮ ፡ በኢጣሊያ ፡ በግሪክና ፡ በግብፅ ፣ በእስያም ፡ ሲጓዝ ፡ ያየው ፡ ምንድን ፡ ነው ፡ ?
፯ ፡ እነዚህን ፡ የቀድሞ ፡ ዘመን ፡ ፍራሾች ፡ በማየት ፡ ምን ፡ እንማራለን ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፩ ፡ መግቢያ ፡ ይቀጥላል ።

### ስለ ፡ ታሪክና ፡ ጂዎግራፊ ፡ ስለ ፡ ልዩ ፡ ልዩም ፡ ነገሮች ።

፩ ፤ መቸውንም ፡ ታሪክና ፡ ጂዎግራፊ ፡ የሚሉትን ፡ ቃል ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሳትሰሙ ፡ አት ቀሩም ፡ ይመስለኛል ። ታሪክ ፡ ማለት ፡ ዓለም ፡ ከተፈጠረ ፡ ወዲህ ፡ ስለ ፡ ሰው ፡ የሚተረከው ነገር ፡ ነው ። ይኸውም ፡ የሰው ፡ ታሪክ ፡ ሺህ ፡ ዓመት ፡ ከተቀመጠ ፡ ሽማግሌ ፡ ጋር ፡ ይወዳደራል ። ከተሞች ፤ ሲሠሩና ፡ ተመልሰው ፡ ሲናዱ ፡ ፈራር ሰው ፡ ዋና ፡ የከተማ ፡ ፍራሽ ፡ ሲሆኑ ፡ አይቶአል ። ከፍ ፡ ብለውና ፡ ገንነው ፡ የነ በሩትም ፡ ነገዶች ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ተዋርደው ፡ ተስፍራቸው ፡ ሲጠፉ ፡ አይቶአል ። ከብዙ ፡ ዘመናት ፡ ጀምሮ ፡ የሆነውን ፡ ሁሉ ፡ የሚያስገርመውን ፡ ታሪክ ፡ ተቀምጦ ሊነግር ፡ እንደሚፈልግ ፡ ሽማግሌ ፡ ነው ።

፪ ፤ ፊት ፡ እንደ ፡ ተናገርሁ ፡ ጂዎግራፊ ፡ ማለት ፡ የከተሞችን ፤ የወንዞችን ፡ የተራሮች ንና ፡ የአገሮችን ፤ እንዲያውም ፡ መንገደኛ ፡ ካንዱ ፡ ወደ ፡ አንዱ ፡ አገር ፡ ሲጓዝ ፡ ያየውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ሁኔታ ፡ የሚያሳይ ፡ ማለት ፡ ነው ። እንግዲያውስ ፡ ጂዎግ ራፊ ፡ ዓለምን ፡ ከዞረ ፡ ሰው ፡ ጋር ፡ ይፎካከራል ። በመርከብ ፡ በሠረገላ ፤ በጀልባ ፡ ወይም ፡ በባቡር ፡ ተቀምጦ ፡ ዓለምን ፡ ዞሮ ፡ አይቶ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ተመልሶ ፡ ያየ ውን ፡ ሁሉ ለኛ ፡ እንደሚነግረን ፡ ሰው ፡ ይመስላል ።

፫ ፤ ታሪክ ፡ በጊዜው ፡ የሆነውንና ፡ የተደረገውን ፡ ነገር ፡ የሚነግርና ፡ የሚያመለክት መሆኑን ፡ ተመልከቱ ፤ ጂዎግራፊም ፡ ስፍራዎች ፡ ያሉበትን ፡ ያመለክታችኋል ። የቀድሞውን ፡ ለማስተዋል ፡ ከኋለኛው ፡ አንዳች ፡ ማወቅ ፡ ይገባችኋል ። አንድ ፡ አንድ ፡ ጊዜም ፡ በባሉን ፡ ወይም ፡ በመርከብ ፡ አድርጌ ፡ የተረክኋቸው ፡ ታሪኮች ፡ ወደ ፡ ተደረጉበት ፡ ስፍራ ፡ ይገፕችሁ ፡ እኼዳለሁ ።

፬ ፤ ታሪክ ፡ መተረኬን ፡ እያበረታሁ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ የምገፋ ፡ ነኝና ፡ አስቀድሞ ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ተፈጠሩ ፤ እነዚህም ፡ ሰፌ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ሁነው ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ በዙና ፡ በየአገሩ ፡ እንደ ፡ ተናኙ ፤ ታላቅ ፡ ጦርነትም ፡ እያ ደረጉ ፡ ሲዋጉ ፡ የነበሩ ፡ ታላቅ ፡ ነገድና ፡ የከበሩ ፡ ሰዎች ፡ እንደ ፡ ነበሩ ፡ እነግራችኋለሁ ።

፭ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ታሪክ ፡ ሳላበዛ ፡ አስቀድሜ ፡ የምነግራችሁ ፡ ምድር ፡ ክብ ፡ መሆን ዋን ፡ ነው ። ሰዎችና ፡ እንስሶች ፡ በላይዋ ፡ ይኖራሉ ። ምድርም ፡ በየብስና ፡ በባሕር ፡ ተከፍላለች ፤ በመሬቱ ፡ ላይ ፡ ዛፍ ፤ ሣር ፤ ቡቃያ ፤ አበባዎች ፡ ይበ ቅሉበታል ። ሰዎችና ፡ እንስሶች ፡ ይኖሩበታል ። መንደሮችና ፡ ታላላቅ ፡ ከተ ሞችም ፡ ተሠርተውበታል ።

፮ ፤ እንደምታውቁት ፡ ከፍ ፡ ያለው ፡ መሬት ፡ ተራራ ፤ ወይም ፡ ኮረፍታ ፡ ይባላል ። ጐድጓዳውም ፡ ምድር ፡ ሸለቆ ፡ ይባላል ። ይህም ፡ ወንዝ ፡ ያለበት ፡ ነው ። አንድ ፡ አንድ ፡ ጊዜም ፡ በኮረፍቶች ፡ ተከበ ፡ የምታገኙት ፡ የረጋ ፡ ውሃ ፡ ሐይቅ ፡ ይባላል ።

፬ ፤ ምድርም ፡ ከሦስቱ ፡ አንዱ ፡ እጅ ፡ መሬት ፡ ሆኖ ፡ ከሦስቱ ፡ ሁለቱ ፡ እጅ ፡ ውሃ ፡ ነው ። ምድር ፡ ትክክል ፡ ሁና ፡ ከሁለት ፡ ተከፍላለች ። በምዕራብ ፡ ወገን ፡ ያለው ፡ የብስ ፡ የሰሜንና ፡ የደቡብ ፡ አሜሪካ ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል ። በምሥራቅ ፡ ወገን ፡ ያለው ፡ የብስ ፤ ኤውሮጳ ፤ አፍሪካ ፤ እስያ ፡ ይባላል ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ ታሪክ ፡ ማለት ፡ ምንድን ፡ ነው ? ከምንስ ፡ ይወጻደራል ፡ ?
፪ ፤ ጂዎግራፊ ፡ ምንድን ፡ ነው ፡ ?
፫ ፤ የምድር ፡ መልክ ፤ ወይም ፡ ቅርጽ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ? ሰዎችና ፡ እንስሶች ፡ ወዴት ፡ ይኖራሉ ፡ ? የምድር ፡ አከፋፈል ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ? በመሬት ፡ ላይ ፡ የበቀለውስ ፡ ምንድን ፡ ነው ፡ ? በመሬት ፡ ላይ ፡ የሚኖሩት ፡ ምንድን ፡ ናቸው ፡ ? በምድር ፡ ላይ ፡ ምን ፡ ይታነጻል ፡ ?
፬ ፤ ተራራ ፤ ወይም ፡ ኮረፍታ ፡ የሚባለው ፡ እንዴት ፡ ያለው ፡ ነው ፡ ? ሸለቆ ፤ ወንዝ ፤ ባሕር ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ ለይተህ ፡ ተናገር ።
፭ ከምድር ፡ ስንተኛው ፡ እጅ ፡ መሬት ፡ ነው ፡ ? ውሃውስ ፡ ስንት ፡ እጅ ፡ ይሆናል ፡ ? የምድር ፡ አከፋፈል ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ? የምዕራብ ፡ የብስና ፡ የምሥራቅ ፡ የብስ ፡ ሁኔታ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፫ ፡ መግቢያ ፤ ይቀጥላል ።

### ዓለም ፡ የብስ ፡ ባሕር ፡ ተብላ ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ተከፈለች ።

፩ ፤ የምድርን ፡ ፊት ፡ ሁለት ፡ እጅ ፡ የሚሆነውን ፡ ውሃ ፡ ተኝቶበታል ፡ ብያለሁ ። ይኸውም ፡ ውሃ ፡ ሰፊ ፡ የሆነ ፡ የጨው ፡ ባሕር ፡ ነው ። ለዚሁም ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ክፍል ፡ ላለው ፡ ባሕር ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ስም ፡ እንሰጠዋለን ።
፪ ፤ በኤውሮጳና ፡ በአሜሪካ ፡ መኻከል ፡ ያለው ፡ ባሕር ፡ አትላንቲክ ፡ ይባላል ። ይኸም ፡ ስፋቱ ፡ ሦስት ፡ ሺህ ፡ ማይል ፡ ይሆናል ። በአሜሪካና ፡ በእስያ ፡ መኻከል ፡ ያለው ፡ ውቅያኖስ ፡ ፓሲፊክ ፡ ይባላል ። ይኸም ፡ ስፋቱ ፡ ዐሥር ፡ ሺህ ፡ ማይል ፡ ይሆናል ፤ ሌላ ፡ ስም ፡ ያላቸውም ፡ ሌሎች ፡ ታላላቅ ፡ የጨው ፡ ባሕሮች ፡ አሉ ።
፫ ፤ እንደምታውቂት ፡ መርከቦች ፡ ካንዱ ፡ አገር ፡ ተነሥተው ፡ ወደ ፡ ሌላው ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ ይሄዳሉ ። እንዲህ ፡ አድርጎ ፡ የንግድ ፡ ጉዳይ ፡ ይከናወናል ። ነገር ፡ ግን ፡ ሰው ፡ የተባለ ፡ ሁሉ ፡ በምድር ፡ የሚኖር ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ በሚሆነው ፡ ሁሉ ፡ የበለጠውን ፡ ይህ ፡ ታሪክ ፡ ይተርካል ።

፬ ፤ ባራቱ ፡ መዓዝን ፡ ዓለም ፡ ስላሉት ፡ ሕዝብ ፤ ሰዎች ፡ ሲናገሩ ፡ ሳትሰሙ ፡ አትቀሩም ። እነዚህም ፡ ኤውሮጳ ፤ እስያ ፤ አፍሪካ ፤ አሜሪካ ፤ ናቸው ። ከነዚ ህም ፡ በቀር ፡ አያሎች ፡ በውሃ ፡ የተከበቡና ፡ ቍርጥራጭ ፡ የሆኑ ፡ አገሮች ፡ አሉ ፤ እነዚህም ፡ ደሴቶች ፡ ይባላሉ ።

፭ ፤ ከነዚህም ፡ ደሴቶች ፡ አያሎቹ ፡ ፓሲፊክ ፡ በሚባለው ፡ ውቅያኖስ ፡ ይገኛሉ ። በነዚህም ፡ ላይ ፡ እጅግ ፡ ቍጥራቸው ፡ የበዙ ፡ ሕዝብ ፡ ይኖሩባቸዋል ። እነ ዚህም ፡ ደሴቶች ፡ በጠቅላላው ፡ አምስተኛ ፡ የዓለም ፡ ክፍል ፡ ተብለው ፡ ይታ ሰባሉ ። ማለት ፡ ኦሺያኒያ ፡ ተብለው ፡ ይጠራሉ ። ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ዓለምን ፡ ኤውሮጳ ፤ እስያ ፤ አፍሪካ ፤ አሜሪካ ፤ አውስትራልያ ፤ ፖሌኔሲያ ፤ ወይም ፡ ኦሺያኒያ ፡ ብለው ፡ በስድስት ፡ ክፍል ፡ ከፍለውታል ። ስለ ፡ ሆነ ፡ እነዚህ ፡ ሁለቱ ፡ የታወቁት ፡ በኋላ ፡ ነው ።

፮ ፤ አሁን ፡ በነዚህ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ በሆኑ ፡ ዓለማት ፡ የሆነውን ፡ እነግራችኋለሁ ። የም ነግራችሁን ፡ ለማስተዋል ፡ በካርታ ፡ ላይ ፡ የተሰጠውን ፡ መመልከት ፡ ያስፈል ጋቿኋል ። የምንነግራችሁ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አገሮች ፡ ያሉት ፡ በወዴት ፡ በኩል ፡ እንደ ሆኑ ፡ ካርታ ፡ ያመለክታችኋል ።

ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ የምድርን ፡ ፊት ፡ ከሦስት ፡ እጅ ፡ ሁለቱን ፡ እጅ ፡ ከድኖት ፡ ያለ ፡ ታላቁ ፡ ውቅ ያኖስ ፡ የትኛው ፡ ነው ፤ ?

፪ ፤ አትላንቲክና ፡ ፓሲፊክ ፡ የተባሉት ፡ ባሕሮች ፡ የትኞቹ ፡ ናቸው ፡ ?

፫ ፤ ስለ ፡ መርከቦች ፡ ምን ፡ ትላለህ ፡ ? መሬትስ ፡ ምንድን ፡ ነው ፡ ?

፬ ፤ አራቱ፡ መዓዝነ ፡ ዓለም ፡ የተባሉት ፡ ምንድን ፡ ናቸው ፡ ? ደሴት ፡ ምንድን፡ ነው ፡ ?

፭ ፤ ስለ ፡ ውቅያኖስ ፡ እስቲ ፡ ንገረን ፡ ?

ተካርታ ፡ ውስጥ ፡ የሚከተለውን ፡ ጥያቄ ፡ እንድትመልሱልኝ ፡ እፈልጋለሁ ።

በአሜሪካ ፡ ምሥራቅ ፡ በኩል ፡ ያለው ፡ ውቅያኖስ ፡ ማን ፡ የሚባለው ፡ ነው ፡ ?

በስተምዕራብ ፡ በኩል ፡ ያለውን ፡ ማን ፡ ትሉታላችሁ ፡ ?

ስለ ፡ ምን ፡ አሜሪካ ፡ ከሁለት ፡ ተከፈለ ፡ ? ኤውሮጳ ፡ ከአሜሪካ፡ በየት፡ በኩል ነው ፡ ?

አፍሪካ ፡ በየት ፡ በኩል ፡ ነው ፡ ?

አሜሪካ ፡ ከኤውሮጳ ፡ ምን፡ ያህል ፡ ይርቃል ፡ ?

አፍሪካ ፡ የቱን ፡ ያህል፡ ይርቃል ፡ ?

በኤውሮጳ፡ ምዕራብ ፡ በኩል ፡ ማን፡ የሚባለው ፡ ውቅያኖስ፡ ይገኛል ፡ ?

በአፍሪካ ፡ ምዕራብ ፡ ያለው ፡ ውቅያኖስ፡ ማን፡ ይባላል ፡ ?

በአፍሪካና ፡ በእስያ ፡ ደቡብ ፡ ያለው ፡ ምንድን ፡ ነው ፡ ? በእስያ ፡ ምሥራቅ ፡ ማን ፡ አለ ፡ ?

ኤውሮጳ ፡ ከማን ፡ ጋር ፡ ይዋሰናል ፡ ? ከአፍሪካ ፡ በየት ፡ በኩል ፡ ነው ፡ ?
አፍሪካ ፡ ከማን ፡ ጋር ፡ ይዋሰናል ፡ ? አፍሪካ ከእስያ ፡ የሚለይበት ፡ እንዴን ፡ ነው ፡ ?
በአፍሪካና ፡ በኤውሮጳ ፡ መኻከል ፡ የተንጣለለው ፡ ባሕር ፡ ማን ፡ ይባላል ፡ ?
ኤውሮጳንና ፡ እስያን ፡ ባሕር ፡ ይለያቸዋልን ፡ ? ወይስ ፡ ሁለቱም ፡ በመሬት ፡ ግጥ ሚያ ፡ አላቸው ፡ ?
እስያ ፡ ከማን ፡ ጋር ፡ ይዋሰናል ፡ ? ዳርቻውስ ፡ የት ፡ ድረስ ፡ ነው ፡ ? ጣትህን ፡ ቀስ ረህ ፡ ወደ ፡ እስያ ፡ ወደ ፡ ኤውሮጳ ፡ ወደ ፡ አፍሪካ ፡ አሳይ ።

## ምዕራፍ ፡ ፬ ።

### በእስያና ፡ በአፍሪካ ፡ በሌሎችም ፡ አገሮች ፡ ስለሚኖሩ ፡ ሕዝብ ።

፩ ፡ ሌላ ፡ ታሪክ ፡ ሳልጀምር ፡ የምነግራችሁ ፡ እስያ ፡ እጅግ ፡ ሰፊ ፡ አገር ፡ መሆኑን ፡ ነው ። እጅግም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሆኑ ወገኖች ፡ የሚኖሩበትና ፡ ቍጥራቸው ፡ የበዛ ፡ ታላላቅ ፡ ከተሞች ፡ ያሉበት ፡ አገር ፡ ነው ።

፪ ፡ ከነዚህም ፡ ወገኖች ፡ ዋኖቹ ፡ ታርታርስ ፡ የሚባሉት ፡ ናቸው ። እነዚህም ከንዱ ፡ ስፍራ ፡ ተነሥተው ፡ ወደ ፡ ሌላው ፡ እየተዛወሩ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ የሚኖሩ ፡ በድንኳን ፡ ነው ። ጥሩ ፡ ጥሩ ፡ ፈረሶችና ፡ ብዙ ፡ የግመል ፡ መንጋ ፡ ያሉዋቸው ፡ ዐረቦች ፡ በዝሆን ፡ የሚቀመጡ ፡ ለጣዖት ፡ የሚሰግዱ ፡ ህንዶች ፡ ያጌጠና ፡ ያማረ ፡ ቤተ መንግሥት ፡ ያላቸው ፡ ቅኔና ፡ ግጥም ፡ የሚወዱ ፡ ፋርሶች ፡ ሻይ ፡ የምናገኝባቸው ፡ ቺኖችና ፡ በወንበር ፡ ላይ ፡ ከመቀመጥ ፡ ይልቅ ፡ በመከዳ ፡ ላይ ፡ መቀመጥ ፡ የሚወዱ ፡ ቱርኮች ፡ እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ አብረው ፡ በንድነት ፡ በበረሃ ፡ ይኖራሉ ።

፫ ፡ የእስያ ፡ ሕዝብ ፡ ቍጥራቸው ፡ ፰፻፸፩ ፡ ሚሊዮን ፡ ይሆናሉ ። በዓለም ፡ ካሉት ፡ ሕዝብ ፡ ከግማሹ ፡ ይበልጣሉ ። ማለት ፡ የሰሜንና ፡ የደቡብ አሜሪካን ፡ ሕዝብ ፡ በንድነት ፡ ደምሮ ፡ ያን ፡ ያህል ፡ ዐሥር ፡ ጊዜ ፡ ማለት ፡ ነው ።

፬ ፡ እንደምታውቁት ፡ አፍሪካ ፡ የጥቍሮች ፡ አገር ፡ ነው ። ሰፋፊ ፡ ከተሞች ፡ አሉበት ። የባላገሮቹ ፡ ቍጥር ፡ ፻፩ ፡ ሚሊዮን ፡ ይሆናል ።

፭ ፡ ኤውሮጳ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ነገድ ፡ ተከፋፍሎአል ። እነዚህም ፡ እንግሊዝ ፡ ፈረንሳይ ፡ ኢጣሊያ ፡ እስጳን ፡ ጀርመን ፡ ረሺያንስ ፡ (መስኮብ) ሌሎችም ፡ ናቸው ። አያሎች ፡ ያማሩና ፡ ያጌጡ ፡ ከተሞች ፡ አሉበት ። የነገዶቹ ፡ ቍጥር ፡ ፫፻፶፰ ሚሊዮን ፡ ይሆናል ።

፮ ፡ አሜሪካ ፡ አያሎች ፡ ታላላቅ ፡ ከተሞችና ፡ ያማሩ ፡ መንደሮች ፡ አሉበት ። ሕዝቡ ፡ በመላው ፡ መቶ ፡ ስድስት ፡ ሚሊዮን ፡ ይሆናሉ ።

፯ ፡ ፊት ፡ እንደ ፡ ተናገርሁት ፡ አሺያኒያ ፣ ተፓሲፊክ ፡ ውቅያኖስ ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ ብዙ ፡ ደሴቶች ፡ አንድነት ፡ ሁነው ፡ ነው ። ከነዚህም ፡ አንዱ ፡ አውስትራልያ ፡ የሚባለው ፡ በዓለም ፡ ሰፊ ፡ ደሴት ፡ የተባለው ፡ ነው ። በነዚሁ ፡ ደሴቶች ፡ ውስጥ ፡ የሚኖሩ ፡ ሕዝብ ፡ ሁልግዜ ፡ እየበዙ ፡ ይሄዳሉ ። አሁን ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ሚሊዮን ፡ ተኩል ፡ ደርሰዋል ፡ ይባላል ።

## ጥያቄ ።

፩ ፡ ስለ ፡ እስያ ፡ ተናገር ።
፪ ፡ ከእስያ ፡ ዋኖቹ ፡ ማን ፡ ይባላሉ ፡ ?
፫ ፡ የእስያ ፡ ሕዝብ ፡ ቍጥራቸው ፡ ስንት ፡ ነው ፡ ?
፬ ፡ የአፍሪካ ፡ ባላገሮች ፡ ቍጥራቸው ፡ ስንት ፡ ነው ፡ ?
፭ ፡ የኤውሮጳ ፡ ባላገሮች ፡ ቍጥራቸው ፡ ስንት ፡ ነው ፡ ?
፮ ፡ የአሜሪካን ፡ ሁኔታ ፡ ንገር ።
፯ ፡ የአሺያኒያ ፡ ደሴት ፡ ከሊቨርፑል ፡ በወዴት ፡ በኩል ፡ ይመስልሃል ፡ ? የባላገሮቹ ፡ ቍጥር ፡ ስንት ፡ ይሆን ?

የአሺያኒያ ፡ ደሴቶች ፡ በወዴት ፡ በኩል ፡ ናቸው ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፭ ፡ መግቢያ ፡ ይቀጥላል ።

### በዓለም ፡ ስላ ፡ አሉ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሕዝብ ።

፩ ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡ የሚኖሩ ፡ ሕዝብ ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ሺህ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ሚሊዮን ፡ ሳይሆኑ ፡ አይቀሩም ። እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ (በኤድን ፡ ) በገነት ፡ አታክልት ፡ ውስጥ ፡ ይኖሩ ፡ የነበሩት ፡ የአዳምና ፡ የሔዋን ፡ ዘሮች ፡ ናቸው ፡ እያለ ፡ ቅዱስ ፡ መጽሐፍ ፡ ይነግረናል ። ከነዚህ ፡ ከሁለቱ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ታላቅ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ወጣ ። !

፪ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ማለት ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ብዛት ፡ እስቲያገኝ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ እንደ ሚፈጅበት ፡ ሳታምኑ ፡ አትቀሩም ።

፫ ፡ ወደ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አገር ፡ ብትሄዱ ፡ የየአገሩ ፡ ሕዝብ ፡ በመልካቸው ፣ ባለባበሳቸው ፡ በናኑዋራቸውም ፡ ልዩነት ፡ እንዳላቸው ፡ ታስተውላላችሁ ።

፬ ፡ እኩሌቶቹ ፡ አሜሪካን ፡ ኢንዲያን ፡ እንደሚባሉት ፡ የገረጡ ፡ ናቸው ፣ የወራ ፡ ቅጠል ፡ ይመስላሉ ። እኩሌቶቹም ፡ እንደ ፡ ቺኖች ፡ ብጫ ፡ ይመስላሉ ፣ ሌሎቹም ፡ እንደ ፡ ህንዶች ፡ የቀይ ፡ ዳማ ፡ ናቸው ፣ ደግሞ ፡ ሌሎቹ ፡ እንደ ፡ ሻንቅሎች ፡ ጥቍሮች ፡ ናቸው ። ሌሎቹም ፡ እንደ ፡ እንግሊዞችና ፡ እንደ ፡ አሜሪኮች ፡ ነጮች ፡ ናቸው ።

፭ ፤ ባንዳንዱ ፡ አገር ፡ የጭራሮ ፡ ቤት ፡ አቁመው ፡ ጭቃ ፡ መርገው ፡ ይኖሩበታል ። ኑሮዋቸውም ፡ በቀስትና ፡ በፍላፃ ፡ አውሬ ፡ እያደኑ ፡ ነው ። ይህም ፡ የአረማውያን ፡ አኑዋኑዋር ፡ ይባላል ። አሜሪካን ፡ ኢንዲያን ፡ የተባሉትና ፡ ከአፍሪካም ፡ ሽንቅሎች ፡ እኩሌቶቹ ፤ አያሎችም ፡ ከእስያ ፡ ሕዝብ ፡ አሺያኒያንስ ፡ ማለት ፡ በፓሲፊክ ፡ ውቅያኖስ ፡ ውስጥ ፡ ባሉት ፡ ደሴቶች ፡ የሚኖሩ ፡ ብዙ ፡ ባላገሮችም ፡ ተጨምረው ፡ አራዊት ፡ ሕዝብ ፡ ናቸው ።

፮ ፤ በአንዳንዱ ፡ አገር ፡ ያሉ ፡ ሕዝብ ፡ በደንጊያና ፡ በጭቃ ፡ በተገነባ ፡ ቤት ፡ ይኖራሉ ። ጥቂቶች ፡ መጻሕፍትም ፡ አሉዋቸው ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ቤት ፡ ክርስቲያን ፡ ወይም ፡ የመሰብሰቢያ ፡ ቤት ፡ ያለዚያም ፡ ቤተ ፡ ጣዖት ፡ የላቸውም ። እንደዚህ ፡ ያሉት ፡ ሕዝብ ፡ የሚበዙት ፡ ከአፍሪካ ፡ ሽንቅሎችና ፡ ከእስያ ፡ አያል ፡ ነገዶች ፡ ናቸው ። እነዚህም ፡ በአረመኔነት ፡ የሚኖሩ ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ አረማውያን ፡ ይባላሉ ። ልማዳቸውም ፡ የጭከናና ፡ የአውሬ ፡ ጠባይ ፡ ነው ።

፯ ፤ በአንዳንዱ ፡ አገርም ፡ ባላገሮቹ ፡ በተመሰገነ ፡ ቤት ፡ ይኖራሉ ። ከቶውንም ፡ ሀብታሞቹ ፡ የጠዱ ፡ እልፍኞች ፡ አሉዋቸው ። ሕዝቡ ፡ የተፈጥሮ ፡ ዕውቀት ፡ አላቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ ለማንበብና ፡ ጥቂት ፡ ለመጻፍ ፡ ያህል ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ስለ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ጕዳይ ፡ ደካሞች ፡ ናቸው ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ አሳብ ፡ የሠለጠኑ ፡ ሕዝብ ፡ የተባሉት ፡ እንኳ ፡ ሳይቀሩ ፤ ቺኖች ፤ ህንዶች ፤ ቱርኮች ፡ ከእስያም ፡ ነገዶች ፡ ክፍል ፡ ከአፍሪካም ፡ ባላገሮችና ፡ ከኤውሮጳ ፡ ወገኖች ፡ እንደዚሁ ፡ እኳኋን ፡ ነበሩ ።

፰ ፤ በኤውሮጳ ፡ በብዙ ፡ ስፍራና ፡ በዩናይትድ ፡ እስቴትስ ፡ ሕዝቡ ፡ በመልካም ፡ ቤቶች ፡ ይኖራሉ ። ያማረ ፡ የቤት ፡ መሣሪያ ፤ አያሎች ፡ መጻሕፍት ፤ መልካም ፡ የትምህርት ፡ ቤቶች ፤ ቤተ ፡ ክርስቲያኖች ፤ የሕዝብ ፡ መሰብሰቢያ ፡ ቤቶች ፤ መርከቦችና ፡ የባቡር ፡ መንገዶች ፡ አሉዋቸው ። እነዚህ ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ሥልጣኔ ፡ የሚኖሩ ፡ ናቸው ።

፱ ፤ እንግዲህ ፡ ሰው ፡ የተባለ ፡ በአራት ፡ ክፍል ፡ እንደ ፡ ተከፈለ ፡ ልብ ፡ አድርጉ ፤ ፊተኞቹ ፡ አረማውያን ፡ ናቸው ፤ ቀጥለው ፡ አራዊት ፡ ሕዝብ ፤ ሦስተኞቹ ፡ የሠለጠኑ ፡ ሕዝብ ፡ ይበላሉ ። ፬ኛ ፡ ላይኖች ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ሥልጣኔ ፡ ያላቸው ፡ ናቸው ። ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጻፈው ፡ ደኅና ፡ አድርጎ ፡ ያስረዳችኋልና ፡ ዋናውን ፡ ነገር ፡ ልብ ፡ አድርጉ ።

## ጥያቄ ።

፩ ፤ በዓለም ፡ ላይ ፡ ያሉት ፡ ሕዝብ ፡ ቍጥር ፡ ስንት ፡ ነው ፡ ?
፪ ፤ አዳምና ፡ ሔዋን ፡ ወዴት ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ፡ ?
፫ ፡ ወደ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ስለ ፡ መሄድ ፡ ምን ፡ ትላለህ ፡ ?
፬ ፤ በአውሬነት ፡ የሚኖሩት ፡ እንዴት ፡ ያሉ ፡ ሕዝብ ፡ ናቸው ፡ ?
፭ ፤ በአረመኔነት ፡ የሚኖሩት ፡ እንዴት ፡ ያሉት ፡ ናቸው ፡ ?
፮ ፤ ሥልጣኔ ፡ ያላቸው ፡ የትኞች ፡ ናቸው ፡ ?
፯ ፤ ላይኖች ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ሥልጣኔ ፡ ያላቸው ፡ የትኞች ፡ ናቸው ፡ ?
፰ ፤ በዓለም ፡ ያሉ ፡ ሕዝብ ፡ በስንት ፡ ይከፈላሉ ፡ ?

## ምዕራፍ ፯ ፡ እስየ ፡ ይቀጥላል ።

### ስለ ፡ እስያ ፡ አየርና ፡ ፍሬ ተራራ ፤ ሕዝብና ፡ እንስሳ ፡ ሌላም ነገር ።

፩፤ ብዙ ፡ ታላላቅ ፡ ከተሞችና ፡ የሰው ፡ ብዛት ፡ ያለበት ፡ ሰፊው ፡ አገር ፡ እስያ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አስቀድሜ ፡ ተናግሬአለሁ ። ይኸውም ፡ አገር ፡ ያለው ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ ባሉት ፡ አገሮች ፡ ክፍል ፡ ነው ። መልከም ፡ ተስፋ ፡ የተባለውን ፡ አገር ፡ ዙራችሁ የህንድን ፡ ውቅያኖስ ፡ አቋርጣችሁ ፡ በመርከብ ፡ ብትሄዱ ፤ ወይም ፡ በኤውሮጳ ፡ አድርጋችሁ ፡ ብታቋርጡ ፤ ያለዚያ ፡ ደግሞ ፡ በኤውሮጳና ፡ በአፍሪካ ፡ መኻከል ፡ ባለው ፡ በሜዴቴራኒያን ፡ ባሕር ፡ አድርጋችሁ ፡ ብትሻገሩ ፡ ወደዚያ ፡ አገር ፡ ለመድረስ ፡ ትችላላችሁ ።

፪፤ በደቡብ ፡ በኩል ፡ ያለው ፡ የእስያ ፡ አገር ፡ አየሩ ፡ ሙቀት ፡ ያለው ፡ ነው ። በዚሁ ፡ ክፍል ፡ የሚኖሩት ፡ ቺኖች ፤ ህንዶች ፤ ፋርሶች ፤ ዐረቦችና ፤ ቱርኮች ፡ ናቸው ። አገሩ ፡ በብዙ ፡ ሰፍራ ፡ ለም ፡ ነው ። በረባዳው ፡ አገር ፡ ያማሩ ፡ አበቦች ፤ ቅመ ማቅመም ፡ የሚሆኑ ፡ ቍጥቋጦችና ፡ ሽታቸው ፡ የሚጣፍጥ ፡ ዛፎች ፡ ይገኛሉ ። በደኑና ፡ በሜካው ፡ ውስጥ ፡ ለማየት ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኙና ፡ ያማሩ ፡ የዱር ፡ አዕዋፍ ፡ ሁልጊዜ ፡ ይታያሉ ።

፫፤ ፒኮክስ ፡ የተባለው ፡ ዎፍ ፡ ለማየት ፡ ያማረ ፡ ነው ፤ በተቀረ ፡ የቤት ፡ አዕዋፍ ፡ ለምንላቸው ፡ ለዶሮና ፡ ለተርኪ ፡ ለሌሎችም ፡ ሁሉ ፡ በውነት ፡ ይህ ፡ ሙቀታሙ ፡ አውራጃ ፡ አገራቸው ፡ ነው ። በኸረ ፡ ሎሚ ፡ በንዳንድ ፡ ስፍራ ፡ በዱር ፡ እየበቀለ ፡ ይገኛል ። የምናውቃቸው ፡ አበቦች ፡ ሁሉ ፡ በደቡብ ፡ እስያ ፡ በቈላው ፡ አገርና ፡ በየጋራው ፡ ላይ ፡ በቅለው ፡ ይታያሉ ።

፬፤ በመኻከል ፡ እስያ ፡ ራሶቻቸው ፡ ዘላለም ፡ በበረዶ ፡ የተሸፈኑ ፡ ተራሮች ፡ አሉ ። በርዝመታቸውና ፡ በከፍታቸው ፡ በዓለም ፡ የታወቁ ፡ ናቸው ። ከፍታቸው ፡ ስድስት ፡ ማይል ፡ ይሆናል ። ከነዚሁ ፡ ተራሮች ፡ በስተሰሜን ፡ ሰፊ ፡ ሜዳ ፡ የሚገኝበት ፡ ብርዳም ፡ አገር ፡ አለ ። ታርታር ፡ የተባሉ ፡ ነገዶች ፡ ግመሎቻቸውንና ፡ ፈረሶቻቸውን ፡ እያዘዋወሩ ፡ ያሰማሩበታል ።

፭፤ በዚሁ ፡ ጭጋግ ፡ ባለው ፡ አገር ፡ ጥቂቶች ፡ መንደሮችና ፡ ከተሞችም ፡ ተሠርተዋል ። ባላገሮቹ ፡ ቤት ፡ የማይሠሩ ፤ በድንኳን ፡ የሚኖሩ ፤ ዘዋሪዎች ፡ ናቸው ። በሚያረቡዋቸው ፡ መንጎች ፡ ሥጋና ፡ ወተት ፡ ይኖራሉ ። በውራጃቸው ፡ የሚገኙትን ፡ አጋዘኖችና ፡ የሜዳ ፡ ፍየሎችን ፡ ሌሎችንም አራዊት ፡ ማደን ፡ ይወዳሉ ።

፮፤ በእስያ ፡ የሚገኙት ፡ እንስሶች ፡ ብዙዎቹ ፡ የታወቁ ፡ ናቸው ። ዝሆን ፡ ጥቅጥቅ ፡ ባለው ፡ ደን ፡ ይገኛል ። አውራሪስም ፡ በወንዝ ፡ ዳር ፡ ይገኛል ። አንበሳ በሜዳ ፡ ሮያል ፡ ታይገር ፡ (ዳልግ ፡ አንበሳ ፡ ) የሚባለው ፡ አውሬ ፡ በደን ፡ ይገኛል ። ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዐይነት ፡ ዝንጀሮችና ፡ ጦጦች ፡ በሙቀታሙ ፡ አውራጃ ፡ ሞልተዋል ። ከቶውንም ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜስ ፡ ቁመታቸው ፡ ሠላሳ ፡ ፈት ፡ የሚሆን ፡ ይገኛሉ ።

፯፤ በደቡብ ፡ እስያ ፡ በኩል ፡ መቸውንም ፡ ዐውሎ ፡ ነፋስ ፡ እየተነሣ ፡ ቤቶችን ፡ ገለ
ባብጦ ፡ ደኑን ፡ ሁሉ ፡ አመሳቅሎ ፤ ማናቸውንም ፡ ነገር ፡ ፍርስርስ ፡ አድርጎ ፡
ምድረ ፡ በዳ ፡ ያደርገዋል ። አገሩን ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ድርቅ ፡ እያሳረረው ፡ ይራባል ።
አንድ ፡ አንድ ፡ ጊዜም ፡ ለሰውና ፡ ለእንስሳ ፡ የሚሆነው ፡ አንዳች ፡ ነገር ፡ እንኳን ፡
ሳይቀር ፡ አንበጣ ፡ መጥቶ ፡ አገሩን ፡ ግጦት ፡ ይሄዳል ። ሕዝቡን ፡ መቅሠፍት ፡
እየጐበኛቸው ፡ ብዙ ፡ ሺህ ፡ ሰዎች ፡ ተጠርገው ፡ ይቀራሉ ።

፰፤ በጂዎግራፊው ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ በታሪኩ ፡ እስያ ፡ እንዲህ ፡ የሚያስደንቅ ፡
አገር ፡ ነው ። ከአራቱ ፡ አህጉር ፡ እስያ ፡ ይሰፋል ። ከፍ ፡ ያሉ ፡ ተራሮች ፡ አሉበት ።
ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዐይነት ፡ እንስሳ ፡ ይረባበታል ። አታክልትም ፡ ይገኝበታል ። ወራቱም ፡
አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ መልካም ፡ ይሆናል ፤ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ይከፋል ።

፱፤ ከዓለም ፡ ሁሉ ፡ ሕዝብ ፡ የሚበዛበት ፡ እስያ ፡ ነው ። ዛሬ ፡ ዓለምን ፡ የመላው ፡
ሰው ፡ መጀመርያ ፡ ተራብቶ ፡ የቈየው ፡ በዚያ ፡ ነው ። ስለ ፡ ሰው ፡ ታሪክ ፡
አንድ ፡ ትልቅ ፡ ነገር ፡ የሆነው ፡ በዚሁ ፡ አገር ፡ ነው ። ከቶ ፡ በዓለም ፡ ተወ
ልዶ ፡ የማያውቅ ፡ አንድ ፡ የሚያስገርም ፡ ሰውነት ፡ በዚሁ ፡ አገር ፡ ተወልዷል ።
ዳግሞ ፡ በዚሁ ፡ ስፍራ ፡ የየሆዋ ፡ ትልቅ ፡ ተአምራት ፡ ተሠርቶአል ።

## ጥ ያ ቄ ።

እስያ ፡ በሰሜን ፤ በምሥራቅ ፤ በደቡብና ፡ በምዕራብ ፡ እንዴት ፡
ይዋሰናል ፡ ?
እስያ ፡ ከኤውሮጳ ፡ በወዴት ፡ በኩል ፡ ነው ፡ ?
ፋርስ ፡ የሚገኘው ፡ ከእስያ ፡ በየትኛው ፡ ክፍል ፡ ነው ፡ ?
ከፋርስ ፡ በየት ፡ በኩል ፡ ብትሄድ ፡ ዐረብ ፤ ሀንዱስታን ፤ ቺን ፤ ታርታር ፤
ሲቤርያ ፤ ቀይ ፡ ባሕር ፡ ግብፅ ፤ የሜዴቴራኒያን ፡ ባሕር ፡ ይገኛሉ ፡ ?
ኤፍራጥስ ፡ የተባለው ፡ ታላቁ ፡ ወንዝ ፡ ከእስያ ፡ በወዴት ፡ በኩል ፡ ይገኛል ፡ ?

፩ ፤ እስያ ፡ ምንድን ፡ ነው ፡ ? እስያ ፡ በወዴት ፡ በኩል ፡ ነው ፡ ?
በየት ፤ በኩል ፡ ብትሄድ ፡ ታገኘዋለህ ፡ ? በጣትህ ፡ አመልክተኝ ።

፪ ፤ በደቡብ ፡ እስያ ፡ አየሩ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?
በደቡብ ፡ እስያ ፡ የሚኖሩ ፡ ሕዝብ ፡ እንዴት ፡ ያሉ ፡ ናቸው ፡ ? በአገሩ ፡
የሚገኘው ፡ ነገር ፡ ምንድን ፡ ነው ፡ ?

፫፤ አዕዋፉ ፤ የሚያበቅለው ፡ ፍራፍሬውና ፡ አበባው ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?

፬፤ ስለ ፡ ተራራው ፡ በሰሜን ፡ እስያም ፡ ስለሚገኘው ፡ ሁሉ ፡ ተናገር ።

፭፤ ባላገሮቹ ፡ እንዴት ፡ ያሉ ፡ ናቸው ፡ ?

፮፤ በእስያ ፡ ስለሚገኙ ፡ እንስሶች ፤

፯፤ ስለ ፡ ደቡብ ፡ እስያ ፤

፰፤ እስያ ፡ በጂዎግራፊው ፡ ልዩ ፡ መሆኑ ፡ ስለ ፡ ምንድን ፡ ነው ፡ ?

፱፤ እስያ ፡ በታሪኩ ፤ ልዩ ፡ መሆኑ ፡ ስለ ፡ ምንድን ፡ ነው ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፤ ፡ እስያ ፡ ይቀጥላል ።

### ስለ ፡ ዓለም ፡ ፍጥረትና ፡ የጥፋት ፡ ውሃ ።

፩ ፤ መጀመርያ ፡ ከዓለም ፡ ክፍል ፡ ሰው ፡ የነበረበት ፡ እስያ ፡ ነበር ። ሁለተኛው ፡ አፍሪካ ፡ ነው ። ከዚያ ፡ ቀጥሎ ፡ ኤውሮጳ ፡ በመጨረሻ ፡ አሜሪካ ፡ ነው ። እነዚያ ፡ የኋለኞች ፡ እንዲያን ፡ የተባሉት ፡ ሕዝብ ፡ ወደ ፡ አሜሪካን ፡ የገቡበትን ፡ ጊዜ ፡ አናውቅም ። ነገር ፡ ግን ፡ ነጮች ፡ ወደ ፡ አሜሪካ ፡ የገቡበት ፡ ከሦስት ፡ መቶ ፡ ሰባ ፡ ዓመት ፡ ወዲህ ፡ ነው ።

፪ ፤ አሁን ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ ፍጥረት ፡ እንመለስ ። ይህ ፡ የሚያስገርም ፡ ነገር ፡ የሆነው ፡ ከስድስት ፡ ሺህ ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ ነው ። የዚህም ፡ ታሪክ ፡ በኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፡ በመጀመርያው ፡ ምዕራፍ ፡ ተመልክቶ ፡ ተነግሮአል ።

፫ ፤ አዳምና ፡ሔዋን ፡ በእስያ ፡ በኤድን ፡ (በገነት) ተክል ፡ መኻከል ፡ ተቀመጡ ። ይህም ፡ ስፍራ ፡ በእስያ ፡ ምዕራብ ፡ ወገን ፡ ካለው ፡ ከኤፍራጥስ ፡ ወንዝ ፡ ሩቅ ፡ አልነበረም ። ነገር ፡ ግን ፡ እግዚአብሔርን ፡ በድለው ፡ በኃጢአት ፡ ከወደቁ ፡ በኋላ ፡ ያነን ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ስፍራ ፡ ለቀቁ ።

፬ ፤ በዚች ፡ ሰፊ ፡ ዓለም ፡ ለጊዜው ፡ የነበሩባት ፡ ከሰው ፡ ወገን ፡ አዳምና ፡ ሔዋን ፡ ብቻ ፡ ነበሩ ። ይህም ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ እግዚአብሔር ፡ አልተለያቸውም ፡ ነበርና ፡ ብቻኑ ታቸው ፡ አይሰማቸውም ፡ ነበር ። ወዲያው ፡ ልጆች ፡ እየተወለዱላቸው ፡ ዘራ ቸው ፡ እየተባዛ ፡ ሄዶ ፡ እነዚህም ፡ በኤፍራጥስ ፡ ዙሪያ ፡ ያለውን ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ መኖሪያቸው ፡ አደረጉት ። በዚያም ፡ ከተሞችንና ፡ መንደሮችን ፡ ሠሩ ። ነገር ፡ ግን ፡ ክፋታቸው ፡ እየበዛ ፡ ስለ ፡ ሄደ ፡ አምላካቸውን ፡ ማምለክ ፡ ረስተው ፡ ክፋ ትንና ፡ አውሬነትን ፡ ተከተሉ ።

፭ ፤ ስለዚህ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ ለማይታዘዙ ፡ እምቢተኞች ፡ ቅጣት ፡ ወደ ፊት ፡ ለሚመጡት ፡ ነገድ ፡ ጥንቃቄ ፡ እንዲሆናቸው ፡ ብሎ ፡ ከኖኅና ፡ ከልጆቹ ፡ በቀር ፡ የሰውን ፡ ወገን ፡ ሁሉ ፡ ለማጥፋት ፡ ቊርጥ ፡ ዐሳብ ፡ አደረገ ።

፮ ፤ ኖኅ ፡ ገና ፡ አስቀድሞ ፡ ጥፋት ፡ እንደሚመጣ ፡ ዐውቆ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ መርከብ ፡ ሠራ ፡ በዚህም ፡ መርከብ ፡ ልጆቹንና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዐይነት ፡ የሆኑ ትን ፡ የምድርን ፡ እንስሳትን ፡ ሁሉ ፡ ጥንድ ፡ እያደረገ ፡ ሰበሰባቸው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ምድር ፡ በመላዋ ፡ በዝናም ፡ ውሃ ፡ እስክትሸፈን ፡ ድረስ ፡ ይዘንም ፡ ጀመር ።

፯ ፤ እንዲህ ፡ ሆኖ ፡ የሰው ፡ ወገን ፡ ሁሉ ፡ ጠፋና ፡ እንደ ፡ ገና ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ የአንድ ፡ ሰው ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ብቻ ፡ ቀረ ። ይህም ፡ የሆነው ፡ ፲፮፻፶፮ ፡ ዓመት ፡ ከዓለም ፡ ፍጥረት ፡ በኋላ ፡ ነው ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ መጀመርያ ፡ ሕዝብ ፡ የነበረበት ፡ በየትኛው ፡ የዓለም ፡ ክፍል ፡ ነው ፡ ?
ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ በየትኛው ፡ ክፍል ፡ ሕዝብ ፡ ሰፈረ ፡ ?
ቀጥለው ፡ ደግሞ ፡ በየት ፡ ሰፈሩ ፡ ? በመጨረሻ ፡ ሕዝቡ ፡ በየት ፡ ክፍል ፡ ሰፈሩ ፡ ?
ህንዶች ፡ መጀመርያ ፡ ወደ ፡ አሜሪካ ፡ የገቡት ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ?
ነጮች ፤ አሜሪካ ፡ የገቡት ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ?

፪ ፤ ዓለም ፡ ከተፈጠረ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ዘመን ፡ ይሆናል ።
በአሪት ዘፍጥረት ፡ በመጀመርያው ፡ ምዕራፍ ፡ እንደ ፡ ተነገረ ፡ አድርገህ ፡ የፍጥረትን ፡ ታሪክ ፡ ተርክልን ።

፫ ፤ አዳምና ፡ሔዋን ፡ ወዴት ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ፡ ?
ከዚያ ፡ ከነበሩበት ፡ ስፍራ ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ ወጥተው ፡ ሄዱ ፡ ?
የኤፍራጥስ ፡ ወንዝ በየት በኩል ፡ ነው ፡ ?

፬ ፤ የአዳምና ፡ የሔዋን ፡ ልጆች ፡ ወዴት ፡ ሰፈሩ ? ምንስ ፡ አደረጉ ፡ ?
እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ ምን ፡ ለማድረግ ፡ ዐሰበ ፡ ?
ስለምን ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰውን ፡ ለማጥፋት ፡ ዐሰበ ፡ ?

፭ ፤ ኖኅ ፡ ምን ፡ አደገረ ፡ ? ስለ ፡ ጥፋት ፡ ውሃ ፡ ተርክልን ።

፮ ፤ የጥፋት ፡ ውሃ ፡ ያደረገው ፡ ምንድን ፡ ነው ፡ ?
የጥፋት ፡ ውሃ ፡ የሆነው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፫ ፡ እስያ ፡ ይቀጥላል ።

### ኖኅና ፡ ልጆቹ ፡ ከመርከብ ፡ እንደ ፡ ወጡ ።

### ሕዝቡ ፡ ሰናዖር ፡ በሚባለው ፡ ስፍራ ፡ እንደ ፡ ሰፈሩ ።

### ስ ለ ፡ ባ ቢ ሎ ን ፡ ግ ን ብ ።

ከጥፋት ፡ ውሃ ፡ በፊት ፡ የነበሩት ፡ ሕዝብ ፡ አንቲዴሉቪያን ፡ ይባላሉ ። ከጥፋት ፡ ውሃ ፡ በፊት ፡ የነበሩ ፡ ማለት ፡ ነው ። ስለነርሱ ፡ በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ከተነገረው ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ አናውቅም ። ምናልባት ፡ በእስያ ፡ ውስጥ ፡ በትንሽ ፡ ስፍራ ፡ ተበትነው ፡ ይሆናል ፡ እንጂ ፡ ከጥፋት ፡ ውሃ ፡ በፊት ፡ በአፍሪካ ፤ በኤውሮጳና ፡ በአሜሪካ ፡ ከቶ ፡ ምንም ፡ ሰው ፡ አልነበረበትም ።

፩ ፤ የጥፋት ፡ ውሃ ፡ መዝነሙን ፡ በኅዳር ፡ ጀምሮ ፡ በመጋቢት ፡ እንዳቆመ ፡ ይታሰባል ። ወዲያው ፡ ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ ውሃው ፡ እየጐደለ ፡ ሄደ ። የኖ

ኅም ፡ መርከብ ፡ በአርመን ፡ አገር ፡ በአንድ ፡ ረጅም ፡ ተራራ ፡ ጫፍ ፡ ላይ ፡ ዐረፈ ። ይህም ፡ ተራራ ፡ አራራት ፡ ይባላል ፡ እስከ ፡ ዛሬም ፡ ድረስ ፡ ይታያል ።

፫ ፡ ኖኅ ፡ ከቤተ ፡ ሰቡና ፡ ከእንስሶቹ ፡ ጋር ፡ ሆኖ ፡ ከመርከብ ፡ ወጣ ። ከነዚህም ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ዓለም ፡ በሕዝብ ፡ ተመላች ። እንስሶቹም ፡ በገዛ ፡ ራሳቸው ፡ ወደ ሩቅ ፡ እየሄዱ ፡ ተናኙ ። ከብዙ ፡ መቶ ፡ ዓመታት ፡ በኋላ ፡ በያገሩ ፡ ገቡበት ።

፬ ፡ ለኖኅ ፡ ሦስት ፡ ልጆች ፡ ነበሩት ። እነርሱም ፡ ሴም ፡ ካም ፡ ያፌት ፡ ናቸው ። እነዚህ ፡ ከቤተ ፡ ሰቦቻቸው ፡ ጋር ፡ ሰናዖር ፡ ወደተባለው ፡ አገር ፡ ገቡ ። ይኸውም ፡ አገር ፡ በካርታ ፡ እንደ ፡ ተመለከተው ፡ በኤፍራጥስና ፡ በጤግሮስ ፡ ወንዞች ፡ አጠገብ ፡ ከአራራት ፡ ተራራ ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ ያለው ፡ አገር ፡ ነው ።

፭ ፡ ምናልባት ፡ ከጥፋት ፡ ውሃ ፡ በፊት ፡ የነበሩ ፡ ሰዎች ፡ (ሰብአ ፡ ትካት ፡) የሰፈሩት ፡ በዚህ ፡ በኤፍራጥስ ፡ ወንዝ ፡ ዳር ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ። የቀድሞ ፡ ወገኖች ፡ መጀመርያ ፡ ነገድ ፡ የሆኑበት ፡ በዚህ ፡ ስፍራ ፡ ነው ።

፮ ፡ ሕዝቡ ፡ በፍጥነት ፡ እየበዙ ፡ ይሄዱ ፡ ጀመር ። ከጥፋት ፡ ውሃ ፡ጀምሮ ፡ መቶው ፡ ዓመት ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፡ ያለ ፡ ልክ ፡ ቍጥራቸው ፡ በዛ ፡ ከኖኅ ፡ ቤተ ፡ ሰቦች ፡ አያሎቹ ፡ እስከዚህ ፡ ዘመን ፡ ነበሩ ። ትውልዳቸውንም ፡ ለልጆቻቸው ፡ ይነግሩዋቸው ፡ ነበር ። ወደ ፡ መርከብ ፡ ከገቡት ፡ በቀር ፡ የጥፋት ፡ ውሃ መጥቶ ፡ ሰውንና ፡ እንስሳን ፡ ሁሉ ፡ እንዳጠፋ ፡ ይተርኩላቸው ፡ ነበር ።

፯ ፡ በጥፋት ፡ ውሃ ፡ የሆነውን ፡ ሁሉ ፡ የሚያስታውሱ ፡ ወይም ወሬውን ፡ የሰሙ ሁሉ ፡ የሰው ፡ ክፋት ፡ ያንኑ ፡ የመሰለ ፡ ቅጣት ፡ እንደ ፡ ገና ፡ መልሶ ፡ ያመጣብናል ፡ እያሉ ፡ ይሠጉ ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ ታላቅ ፡ ግንብ ፡ ለመ/ሥራት ፡ ተማከሩ ። በዚያም ፡ ውስጥ ፡ ገብተው ፡ ሊሰወሩ ፡ ነበር ። ይህም ፡ ግንብ ፡ ባብል ፡ ይባላል ።

፰ ፡ በኤፍራጥ ፡ ወንዝ ፡ ዳር ፡ በስተ ፡ ምሥራቅ ፡ ወገን ፡ የሕንጻውን ፡ መሠረት ፡ ቈፈሩ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ለመድረስ ፡ እንዲመቻቸው ፡ ግንቡን ፡ ከፍ ፡ አድርገው ፡ ለመሥራት ፡ ዐስበው ፡ ነበር ።

፱ ፡ ግንቡን ፡ የሚሠሩት ፡ ፀሓይ ፡ ባደረቀው ፡ ጡብ ፡ ነበር ። ጡቡንም ፡ ሲገነቡ ኖራና ፡ አሸዋ ፡ በመሰለ ፡ ነገር እያያያዙ ፡ ነው ።

፲ ፡ ሠራተኞቹ ፡ በትጋት ፡ ይሠሩ ፡ ነበርና ፡ ጡቡን ፡ አንዱን ፡ በአንዱ ፡ ላይ ፡ እያደራረቡ ፡ ሲገነቡ ፡ ከላይ ፡ ሆነው ፡ ምድሩን ፡ ቍልቍል ፡ ሲመለከቱት ፡ እጅግ ፡ ሩቅ ፡ ሆኖ ፡ እስኪታይ ፡ ድረስ ፡ ያጣድፉ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ሰማዩና ፡ ፀሓዩ ፡ ከዋክብቱም ፡ ርቀታቸው ፡ ግንቡ ፡ ሲጀመር ፡ እንደ ፡ ነበሩ ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ ያራራቃቸው ፡ ሁኔታ ፡ አልተለወጠም ።

ጥ ያ ቄ ።

፩ ፡ ከጥፋት ፡ ውሃ ፡ በፊት ፡ የነበሩት ፡ ማን ፡ ይባላሉ ፡ ?

፪ ፡ የጥፋት ፡ ውሃ ፡ (ማየ ፡ አይኅ ፡) መዝነሙን ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ጀመረና ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ በራ ፡ ?

፫ ፤ የሴም ፡ ልጆች ፡ በኤፍራጥስ ፡ አውራጃ ፡ ያለውን ፡ አገር ፡ እንደ ፡ ተካፈሉ ፡ ይመስላል ። የካም ፡ ልጆች ፡ በምዕራብ ፡ አውራጃ ፡ ያለውን ፡ አገር ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ አፍሪካ ፡ ፈቀቅ ፡ አሉ ። ከዚያ ፡ ምስርን ፡ ያዙና ፡ ታላቅ ፡ ነገድ ፡ ለመሆን ፡ በቁ ። የያፌት ፡ ልጆች ፡ ወደ ፡ ግሪክ ፡ አገር ፡ ፈቀቅ ፡ አሉና ፡ ከዚያ ፡ አያሎችን ፡ የኤውሮጳን ፡ ነገድ ፡ መሠረቱ ።

፬ ፤ በዛሬው ፡ ዘመን ፡ አያሎች ፡ መንገደኞች ፡ በኤፍራጥስ ፡ ወንዝ ፡ ዳር ፡ ሰፋፊ ፡ ኮረፍቶች ፡ አግኝተዋል ። የተሠሩበት ፡ በዝፍትና ፡ በሚያጣብቅ ፡ ነገር ፡ ባንድነት ፡ ተበክቶ ፡ በፀሓይ ፡ በተተኰሰ ፡ ጡብ ፡ ነው ። እነዚህም ፡ ኮረፍቶች ፡ ካራት ፡ ሺህ ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ ተሠርቶ ፡ የነበረ ፡ የባብል ፡ ግንብ ፡ (የጥቅመ ፡ ሰናዖር ፡) ፍራሾች ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ ተረዱት ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ ስለ ፡ ቋንቋቸው ፡ መለያየት ፡ ንገረኝ ።
፪ ፤ በቋንቋቸው ፡ መለያየት ፡ ምን ፡ ተደረገ ፡ ?
፫ ፤ የሴም ፡ ልጆች ፡ እንዴት ፡ ሆኑ ፡ ? የካምና ፡ የያፌት ፡ ልጆች ፡ እንዴት ፡ ሆኑ ፡ ?
፬ ፤ መንገደኞቹ ፡ ያገኙት ፡ ምንድን ፡ ነው ፡ ? ኮረፍቶቹ ፡ ምን ፡ ይመስሉሃል ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፲ ፡ እስያ ፡ ይቀጥላል ።

### ስለ ፤ ታላቋ ፡ የአሶር ፡ መንግሥትና ፡ ስለ ፡ ንግሥት ፡ ሴሚራሚስ ፡ መንግሥ ።

፩ ፤ የተረፉት ፡ የሰው ፡ ወገኖች ፡ ወደ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የዓለም ፡ ክፍሎች ፡ በተበተኑ ፡ ጊዜ ፡ በባቢሎን ፡ ግንብ ፡ ዙሪያ ፡ የቀሩ ፡ ሕዝብ ፡ ስለ ፡ ነበሩ ፡ የሰናዖርን ፡ አውራጃ ፡ ከመያዝ ፡ አላቋረጡም ፡ ነበር ። አገሩ ፡ ሙቀት ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ፍሬያም ፡ ነው ። በጊዜ ፡ ብዛት ፡ እየበረከቱ ፡ ሰፊ ፡ አገር ፡ ያዙና ፡ መንደሮችንና ፡ ከተሞችን ፡ ለመሥራት ፡ ተቻላቸው ።

፪ ፤ አገሩ ፡ አሶር ፡ የመባል ፡ ስም ፡ አገኘ ። ይህም ፡ መጀመርያ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ የሰው ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ ወይም ፡ ወገን ፡ ለመባል ፡ የበቁበት ፡ ነበር ። ዳርቻው ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ዘመን ፡ ይለያያል ። ነገር ፡ ግን ፡ ስፍራው ፡ በፋርስ ፡ ባሕር ፡ ሰሜን ፡ በሁለቱ ፡ ወንዞች ፡ በኤፍሬጥስና ፡ በጤግሮስ ፡ በኩል ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በካርታ ፡ ይታያል ።

፫ ፤ የኖኅ ፡ ታላቁ ፡ ልጁ ፡ አሹር ፡ የተባለው ፡ የአሶር ፡ የመጀመርያ ፡ ገዢ ፡ ነበር ። ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ፪ሺ ፡ ፪፻፳፱ ፡ ዓመት ፡ የነነዌን ፡ ከተማ ፡ ሠራና ፡ መቶ ፡ ፊት ፡ ከፍታ ፡ ያለው ፡ አድርጎ ፡ ዙሪያዋን ፡ በግንብ ፡ ከበባት ። እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ በ፲ሺ ፡ ፭፻ ፡ ግንቦች ፡ እንድትጠበቅ ፡ አደረጋት ። የያንዳንዱ ፡ ግንብ ፡ ቁመት ፡ ፪፻ ፊት ፡ ነበር ። ከተማዪቱ ፡ እጅግ ፡ ሰፊ ፡ ነበረች ፡ ይባላል ። ዙሪያዋን ፡ ለመዞር ፡ መቶ ፡ ማይል ፡ ያስሄዳል ። ከዚችው ፡ ከታላቂቱ ፡ ከተማ ፡ ፍራሽ ፡ ላይ ፡ መንገደኞች ፡ እጅግ ፡ ያማሩ ፡ ከደንጊያ ፡ የተቀረጹ ፡ ምስሎችን ፡ ቈፍረው ፡ እያወጡ ፡ ወደ ፡ እንግሊዝ ፡ አገር ፡ ወስደዋቸዋል ።

፬ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በዚያው ፡ ዘመን ፡ ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፤ የተሠራው ፡ የባቢሎን ፡ ከተማ ፡ በታላቅነትም ፡ በውበትም ፡ ከነነዌ ፡ ከተማ ፡ ይበልጥ ፡ ነበር ። የተሠራውም ፡ በኤፍራጥስ ፡ ወንዝ ፡ ዳር ፡ ነው ። የግንቡ ፡ ውፍረትና ፡ የአርመኑ ፡ ስፋት ፡ በስድስት ፡ ሠረገሎች ፡ በድስት ፡ ፈረሶች ፡ ተጠምደው ፡ ጐን ፡ ለጐን ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ በጫፉ ፡ ላይ ፡ ያስሄዳቸዋል ። በጐንና ፡ በጐኑ ፡ ሠረገሎቹ ፡ አፈት ልከው ፡ ይወድቃሉ ፡ ለማት ፡ አያስፈራም ፡ ነበር ፡ ይባላል ። ዛሬ ፡ በዘመናችን ፡ ከተሞቻችንን ፡ በግንብ ፡ እንከባቸውም ። በጥንት ፡ ዘመን ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሕዝባቸውን ፡ ከጠላት ፡ ለመጠበቅ ፡ ሲሉ ፡ በግንብ ፡ የተከበበ ፡ ቅጽር ፡ ያስፈልጋቸው ፡ ነበር ።

፭ ፤ በዚሁ ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ ደምቆ ፡ የሚታይ ፡ ቤተ ፡ መንግሥትና ፡ አታክልት ፡ ነበረበት ፤ ሳሠራሩም ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ሁኔታ ፡ ነበረው ። ከምድር ፡ ላይ ፡ ሳያርፍ ፡ አየር ፡ ላይ ፡ የተንጠለጠለ ፡ ይመስል ፡ ነበር ። ፍሬ ፡ የሚያፈሩ ፡ ዛፎችና ፡ ብዙ ፡ ዐይነት ፡ አበቦች ፡ ነበሩበት ።

፯ ፤ ደግሞ ፡ ለአሶራውያን ፡ ለዋናው ፡ ጣዖታቸው ፡ ለቤሉስ ፡ (ቤል ፡) ወይም ፡ ለባአል ፡ የተሠራ ፤ ለማየት ፡ እጅግ ፡ ያማረ ፡ ቤተ ፡ ጣዖት ፡ ነበር ። ይህ ፡ ቤተ ፡ ጣዖት ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ቁመቱ ፡ ፯፻፰ ፡ ፊት ፡ ነበር ።በዚሁም ፡ ውስጥ ፡ ከፍታው ፡ ፵ ፡ ፊት ፡ የሚሆን ፡ የጣዖቱ ፡ የቤሉስ ፡ የወርቅ ፡ ምስል ፡ ነበረበት ።

፰ ፤ ይህንንም ፡ የነገርኋችሁን ፡ የባቢሎንን ፡ ከተማ ፡ ቀድሞ ፡ የሠራው ፡ ናምሩድ ፡ ነው ። ስለርሱም ፡ ያ ፡ ኀይለኛው ፡ አዳኝ ፡ ብሎ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ነግሮናል ። ነገር ፡ ግን ፡ አታክልቱንና ፡ ቤተ ፡ መንግሥቱን ፡ ያሠራችው ፡ ሴሚራሚስ ፡ የተባለች ፡ ሴት ፡ ናት ።

፱ ፤ የኒኑስ ፡ የአሶር ፡ ንጉሥ ፡ ሚስት ፡ ነበረች ። ነገር ፡ ግን ፤ ንጉሡ ፡ ኒኑስ ፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፡ ንግሥት ፡ ሴሚራሚስ ፡ ዋና ፡ የመንግሥቱ ፡ ገዢ ፡ ሆነች ። ክብርን ፡ ፈላጊ ፡ ሴት ፡ ስለ ፡ ነበረች ፡ ባቢሎንን ፡ እጅግ ፡ ያማረች ፡ ከተማ ፡ ልታደርጋት ፡ ፈለገች ፡ እንጂ ፡ ዝም ፡ ብላ ፡ መኖር ፡ አልበቃትም ።

፲ ፤ በዓለም ፡ ያሉትን ፡ ነገዶች ፡ ሁሉ ፡ አሸንፋለሁ ፡ ብላ ፡ በክፉ ፡ ምኞት ፡ ተማቀየች ። ልክ ፡ የሌለው ፡ ጦር ፡ ሰበሰበችና ፡ ስሙ ፡ ጥሩውን ፡ እጅግም ፡ ሀብታም ፡ የተባለውን ፡ የህንድን ፡ ንጉሥ ፡ ለመውጋት ፡ ተነሣች ። እርሱም ፡ ዛሬ ፡ ሂንዱስታን ፡ በምንለው ፡ አገር ፡ ይኖር ፡ ነበር ፤ ይህም ፡ አገር ፡ በአሶርያ ፤ በደቡብ ምሥራቅ ፡ በኩል ፡ ያለው ፡ አገር ፡ ነው ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ ሕዝቡ ፡ በቋንቋ ፡ ከተለያዩ ፡ በኋላ ፡ የሰናዖርን ፡ አገር ፡ ለቀቁን ፡ ?
የሰናዖር ፡ ሰዎች ፡ እየበዙ ፡ ሄዱን ፡? እንደምን ፡ ሆኑ ፡ ?
፪ ፤ በሰናዖር ፡ ዙሪያ ፡ ያለው ፡ አገር ፡ ማን ፡ የሚባል ፡ ስም ፡ አገኘ ፡ ?
ከሁሉ ፡ በፊት ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ መንግሥት ፡ ተብሎ ፡ የተጠራው ፡ የትኛው ፡ ነገድ ፡ ነው ፡ ?
አሶር ፡ የሚገኘው ፡ ከፋርስ ፡ ባሕር ፡ በወዴት ፡ በኩል ፡ ነው ፡ ?
ከሜዲቴራኒያን ፡ ባሕር ፡ በወዴት ፡ ነው ፡ ?
ከምስር ፡ በወዴት ፡ በኩል ፡ ይሆናል ፡ ?
፫ ፤ የአሶር ፡ የመጀመሪያው ፡ ንጉሥ ፡ ማን ፡ ነው ፡ ?
የትኛውን ፡ ከተማ ፡ ነው ፡ የሠራ ፡? የነነዌን ፡ ከተማ ፡ አሠራር ፡ ተናገር ።
፬ ፤ የባቢሎን ፡ ከተማ ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ ?
የሚያስደንቀውን ፡ የከተማውን ፡ ሥራ ፡ ተናገር ።
የቀድሞ ፡ ሰዎች ፡ ከተሞቻቸውን ፡ በግንብ ፡ የሚከቡ ፡ ስለምንድር ፡ ነው ፡ ?
፭ ፤ በአየር ፡ ላይ ፡ የተንጠለጠለው ፡ አታክልት ፡ ሥራ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?
፮ ፤ የጣዖቱ ፡ የቤሉስ ፡ መቅደስ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ኑሮዋል ፡ ?

፯ ፤ ባቢሎንን ፡ የመሠረተ ፡ ማነው ፡ ?
በአየር ፡ ላይ ፡ የተንጠለጠለውን ፡ አታክልትና ፡ የቤሉስን ፡ ምስል ፡ የሠራ ፡ ማነው ፤ ?
ሴሚራሚስ ፡ ማናት ፡ ? በባቢሎን ፡ ብቻ ፡ ደስ ፡ ያላት ፡ ኑራለችን ፡ ?
፰ ፤ እንዴት ፡ ያለ ፡ የክፉትና ፡ የስንፉና ፡ ምኞት ፡ ነበራት ፡ ? ምን ፡ አደረገች ፡ ?
የህንድ ፡ ንጉሥ ፡ በየት ፡ በኩል ፡ ይኖር ፡ ኑርዋል ፡ ?
ህንድ ፡ በወዴት ፡ በኩል ፡ ነው ፡ ?
ህንድ ፡ ከአሶር ፡ በወዴት ፡ በኩል ፡ ይገኝ ፡ ይሆን ፡ ?

## ም ዕ ራ ፍ ፡ ፲፩ ፡ እ ስ ያ ፡ ይ ቀ ጥ ላ ል ።

### ንግሥት ፡ ሴሚራሚስ ፡ ዓለምን ፡ ለማሸነፍ ፡ እንደ ፡ ወጣችና ፡ የህንድ ፡ ንጉሥ ፡ ድል ፡ እንዳደረጋት ።

፩ ፤ እጅግ ፡ በለጸጋና ፡ ኀይለኛ ፡ የነበረ ፡ የህንድ ፡ ንጉሥ ፡ አገሩን ፡ ለመውረር ፡ ሴሚራሚስ ፡ እንደ ፡ መጣችበት ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ መክቶ ፡ አገሩን ፡ ለማዳን ፡ ልክ ፡ የሌለው ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ሰበሰበ ። ካርበኞቹም ፡ ሌላ ፡ ደግሞ ፡ አያሎች ፡ ታላላቅ ፡ ዝሆኖች ፡ ነበሩት ።

፪ ፤ የነዚህም ፡ የታላላቆች ፡ ዝሆኖች ፡ የያንዳንዳቸው ፡ ኀይል ፡ የመላውን ፡ ወታደር ፡ ኀይል ፡ ያኽላል ። ጠላት ፡ ወደ ፡ ተሰለፈበት ፡ ገሥግሦ ፡ ጠላትን ፡ በኩምቢው ፡ እያንጠለጠለ ፡ ለማምዘግዘግና ፡ በዚያም ፡ አንዳች ፡ በሚያህለው ፡ እግሩ ፡ ለመዳጥ ፡ ደኅና ፡ አድርጎ ፡ ተምሮአል ።

፫ ፤ ንግሥት ሴሚራሚስ ፡ ዝሆን ፡ አልነበራትምና ፡ የህንድ ፡ ንጉሥ ፡ ሳያሸንፈኝ ፡ አይቀርም ፡ በማለት ፡ ስለ ፡ ፈራች ፡ ይህን ፡ የመጣባትን ፡ መከራ ፡ ከሁን ፡ ቀድም ፡ ባልተደረገ ፡ ነገር ፡ ለመከላከል ፡ ዐስባ ፡ አስቀድማ ፡ ሦስት ፡ ሺህ ፡ በሮች ፡ አሳረደች ።

፬ ፤ ቆዳቸው ፡ ተገፎ ፡ ዝሆን ፡ እየመሰሉ ፡ እንዲሠሩ ፡ አዘዘች ። ይህም ፡ ከሆነ ፡ በኋላ ፡ በግመል ፡ እየተጫኑ ፡ ወደ ፡ ጦርነቱ ፡ ቀርበው ፡ በተደረደሩ ፡ ጊዜ ፡ በውነት ፡ የተሰለፉ ፡ ዝሆኖች ፡ መሰሉ ፡ ያለጥርጥር ፡ ሴሚራሚስ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ዝሆን ፡ ከየት ፡ ስፍራ ፡ አገኘችው ፡ ብሎ ፡ የህንድ ፡ ንጉሥ ፡ ተደነቀ ።

፭ ፤ ጦርነቱ ፡ እንደ ፡ ተጀመረ ፡ የህንድ ፡ ንጉሥ ፡ እውነተኞች ፡ ዝሆኖቹን ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ይዞ ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ ንግሥት ፡ ሴሚራሚስም ፡ በቆዳ ፡ የተሠሩ ፡ ዝሆኖችዋን ፡ በግመል ፡ አስጭና ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ በጀግንነት ተጋፈጠችው ።

፮ ፤ የህንድ ፡ የጦር ፡ አርበኞች ፡ ወደ ፡ አሶራውያን ፡ ሰልፈኞች ፡ ፊት ፡ በተቃረቡ ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ እንኳ ፡ የነሱን ፡ ዝሆን ፡ የሚመስል ፡ አላዩም ። ከዚህ ፡ ወዲያ ፡ ፍርሀትን ፡ ወዲያ ፡ አስወግደው ፡ ወደ ፡ ንግሥት ፡ ሴሚራሚስና ፡ ወደ ፡ አርበኞችዋ ፡ በመናደድ ፡ ገሠገሡባቸው ።

፬ ፤ የህንድ ፡ እውነኞቹ ፡ ዝሆኖች ፡ ግን ፡ የአሶራውያንን ፡ ወታደሮች ፡ በኩምቢያቸው ፡ እያንጠለጠሉ ፡ ወደ ፡ አየር ፡ ያጉኑዋቸው ፡ ጀመር ። መቶ ፡ መቶውን ፡ እየጨበጡ ፡ በእግራቸው ፡ ይደፈጥጡዋቸው ፡ ጀመር ። እንዲህ ፡ ሁነው ፡ የአሶራውያን ፡ ጭፍሮች ፡ ከሥራቸው ፡ ተነቀሉና ፡ የህንድ ፡ ንጉሥ ፡ ፈጽሞ ፡ ድል ፡ አደረጋቸው ።

፭ ፤ ንግሥት ፡ ሴሚራሚስ ፡ ክፉኛ ፡ ቈስላ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ወዲያው ፡ ከሠረገላዋ ፡ ገብታ ፡ ከመዋጊያው ፡ ስፍራ ፡ ተነሥታ ፡ ሸሸች ። ወደኋላዋም ፡ ሸመጠጠች ። ነገር ፡ ግን ፡ በመጨረሻ ፡ በታላቅ ፡ ኀዘን ፡ አምልጣ ፡ ወደ ፡ ግዛትዋ ፡ ደረሰች ።

፮ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ መኖሪያዋን ፡ በባቢሎን ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ አደረገች ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ከአየር ፡ የተንጠለጠለ ፡ በሚመስለው ፡ እጅግ ፡ ያምር ፡ በነበረው ፡ አታክልትዋ ፡ መታጣት ፡ ደስታ ፡ አላገኘችም ። በኋላም ፡ ዙፋንዋን ፡ ለመውረስና ፡ በሕዝቡ ፡ ላይ ፡ ለመንገሥ ፡ ብሎ ፡ ኒንያስ ፡ የተባለው ፡ ልጅዋ ፡ ገደላት ፡ ይባላል ።

፯ ፤ የታላቂቱ ፡ ንግሥት ፡ የሴሚራሚስ ፡ ፍጻሜ ፡ እንዲህ ፡ የሚያሳዝን ፡ ሆኖ ፡ ቀረ ። የገዛ ፡ ሕዝቡዋን ፡ ደስ ፡ ከማሰኘት ፡ ችላ ፡ ብላ ፡ የሌላውን ፡ አገር ፡ ድል ፡ አድርጌ ፡ ሕዝቡን ፡ እገዛለሁ ፡ እያለች ፡ ዘመንዋን ፡ ሙሉ ፡ ስትመኝ ፡ መኖርዋ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ስንፍና ፡ ነው ፡ ? ነገር ፡ ግን ፡ ሌላው ፡ ሊያደርግልህ ፡ እንደምትወደው ፡ አንተም ፡ እንዲሁ ፡ አድርግለት ፡ የተባለውን ፡ አልተማረችም ፡ ኑራለች ።

## ጥያቄ ።

፩ ፡ ሴሚራሚል ፡ ልትዋጋው ፡ መምጣትዋን ፡ የህንድ ፡ ንጉሥ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ምን ፡ አደረገ ? እንዴት ፡ ያለ ፡ ዐይነት ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ኖረዋታል ፡ ?
፪ ፤ ዝሆኖቹ ፡ እንዴት ፡ ያሉ ፡ ነበሩ ፡ ?

፫ ፤ ንግሥት ፡ ሴሚራሚስ ፡ ክህንድ ፡ ንጉሥ ፡ ጋር ፡ በእንዴት ፡ ያለ ፡ አኳኋን ፡ ተከላከልች ፡ ?

፬ ፤ ስለ ፡ ውጊያው ፡ ተናገር ። የጦርነቱ ፡ ጥቅም ፡ ምንድር ፡ ነው ፡ ?
፭ ፤ ሴሚራሚስ ፡ ምን ፡ አደረገች ፡ ?
፮ ፤ በመጨረሻው ፡ እንዴት ፡ ሆነች ፡ ?
፯ ፤ ሴሚራሚስ ፡ ያደረገችው ፡ ሥራ ፡ መልካም ፡ ነውን ፡ ወይስ ፡ ክፉ ፡ ? ደስ ፡ ያላት ፡ ይመስልሃልን ፡ ?
ሰው ፡ ሌላውን ፡ ደስ ፡ ሳያሰኝ ፡ ራሱን ፡ ደስ ፡ ሊለው ፡ ይችላልን ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፲፪ ፡ እስያ ፡ ይቀጥላል ።

### ስለ ፡ ኒንያስ ፡ የሳርዳናፓሎስ ፡ መንግሥና ፡ የአሶራውያን ፡ መንግሥት ፡ መፍረስ ።

፩ ፤ ኒንያስ ፡ እናቱን ፡ ፀክፋት ፡ ከገደለ ፡ በኋላ ፡ የአሶርያ ፡ ንጉሥ ፡ ሆነ ። የነገሠበት ፡ ዘመን ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ሁለት ፡ ሺህ ፡ ዓመት ፡ ወይም ፡ ከጥፋት ፡ ውኃ ፡ በኋላ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ነው ።

፪ ፤ ኒንያስ ፡ ሰነፍም ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ ክፉ ፡ ነበር ፡ ማለት ፡ ብቻ ፡ አይበቃውም ። እንደ ፡ እናቱ ፡ ሌሎቹን ፡ አገሮች ፡ ወግቶ ፡ ለማሸነፍ ፡ አይፈትንም ፡ ነበር ። በቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ውስጥ ፡ ዘግቶ ፡ ምንም ፡ ሳያስብ ፡ ለራሱ ፡ ብቻ ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ ይውል ፡ ነበር ።

፫ ፤ ሕዝቡ ፡ እንደ ፡ ጠላው ፡ ያውቃልና ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ዙሪያ ፡ ሁነው ፡ የሚጠብቁት ፡ ዘበኞች ፡ አቆመ ። ዳሩ ፡ ግን ፡ የራሱን ፡ ዘበኞች ፡ እንኳ ፡ አያምናቸውም ፡ ነበር ። በመጨረሻው ፡ ሰው ፡ ይግደለው ፡ ወይስ ፡ ፀልጋው ፡ ላይ ፡ በሰላም ፡ ይሙት ፡ እንጃ ፡ ታሪክ ፡ አይነግረንም ።

፬ ፤ ኒንያስ ፡ ከነገሠ ፡ ፀኋላ ፡ ፀመኻከል ፡ የገባ ፡ ፻፳ ፡ ዘመን ፡ አሉ ። በዚሁ ፡ ዘመን ፡ ውስጥ ፡ የአሶር ፡ መንግሥት ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ለመናገር ፡ ያስቸግራል ። ምናልባት ፡ በዚያ ፡ ዘመን ፡ ከነገሡት ፡ የሚበዙቱ ፡ እንደ ፡ ኒንያስ ፡ አንዳች ፡ የሚጠቅም ፡ መታሰቢያ ፡ ሳያደርጉ ፡ ጊዜያቸውን ፡ በስንፍናና ፡ በደስታ ፡ አሳልፈውት ፡ ይሆናል ።

፭ ፤ ፑል ፡ አሶር ፡ በነገሠ ፡ ጊዜ ፡ እስራኤላውያንን ፡ ድል ፡ አደረገና ፡ አስገበራቸው ። ይህም ፡ የነነዌ ፡ ንጉሥ ፡ ነበር ፡ ይባላል ። ነቢዩ ፡ ዮናስ ፡ ንስሓን ፡ ለመስበክ ፡ የተላከው ፡ ወደርሱ ፡ ነው ። ይህም ፡ የሆነው ፡ ፰፻፰ ፡ ዓመት ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ነው ።

፮ ፤ ከያሉቹ ፡ ዓመታት ፡ ፀኋላ ፡ ሳርዳናፓሎስ ፡ የተባለ ፡ ንጉሥ ፡ በአሶራውያን ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ ነበር ። እርሱም ፡ እጅግ ፡ መልከ ፡ ቀና ፡ ውበት ፡ ያለው ፡ ሕፃን ፡ ንጉሥ ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ለመንግሥቱ ፡ የማያስብ ፤ ለሕዝቡ ፡ ኑሮ ፡ የማይጣጣር ፤ ዳተኛና ፡ ሰነፍ ፡ ነበረ ።

፯ ፤ ከቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ሳይወጣ ፡ ዘወትር ፡ ከሴቶች ፡ ጋር ፡ ይውል ፡ ነበር ፤ ለሴቶች ፡ ቈንጆ ፡ መስሎ ፡ እንዲታይ ፡ ፊቱን ፡ ይነቀስ ፡ ነበር ፤ ከቶውንም ፡ አንድ ፡

አንድ ፡ ጊዜ ፡ የሴት ፡ ልብስ ፡ ይለብስ ፡ ነበር ። እንደዚህ ፡ ባለ ፡ በሚያሥቅ ፡ ሁኔታ ፡ ታላቁ ፡ ንጉሥ ፡ ሳርዳናፓሎስ ፡ ከሴቶች ፡ ጋር ፡ እየዋለ ፡ ፈትል ፡ መፍተል ፡ ይረዳቸው ፡ ነበር ።

፰ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ሳርዳናፓሎስ ፡ እንደዚሁ ፡ በዓል ፡ ሲያደርግና ፡ ሲጨፍር ፤ ፊቱን ፡ ሲነቀስ ፤ እንደ ፡ ሴት ፡ ሲለብስና ፡ በመፍተል ፡ ሴቶችን ፡ ሲረዳ ፡ ሳለ ፤ በራሱ ፡ ላይ ፡ ታላቅ ፡ ጥፋት ፡ መጣበት ።

፱ ፤ አርባስስ ፡ የሜዶን ፡ ንጉሥ ፡ በዚህ ፡ በማይረባ ፡ ንጉሥ ፡ ላይ ፡ ጦር ፡ ዐወጀና ፡ በባቢሎን ፡ ከተማ ፡ ሳለ ፡ በከበበው ፡ ጊዜ ፡ ሳርዳናፓሎስም ፡ እንደማያመል ጥና ፡ ባርያም ፡ እንደሚያደርገው ፡ አስቀድሞ ፡ ዐወቀ ።

፲ ፤ ባርያ ፡ ከመሆን ፡ መሞትን ፡ መርጦ ፡ የመንግሥቱን ፡ መዝገብ ፡ ሁሉ ፡ በት ልቁ ፡ አዳራሽ ፡ ቈለለና ፡ እሳት ፡ ለቀቀበት ። አዳራሹም ፡ በእሳት ፡ በተያያዘ ፡ ጊዜ ፡ ወዲያው ፡ ሳርዳናፓሎስ ፡ ከመኳንንቱና ፡ ከቁነጃጅቱ ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ነዲዱ ፡ እሳት ፡ ገብቶ ፡ ተቃጥሎ ፡ ሞተ ። የአሶርያ ፡ ንጉሥ ፡ መጨረሻው ፡ እንዲህ ፡ ሆኖ ፡ ቀረና ፡ አገሩንም ፡ አርባስስ ፡ ድል ፡ አድርጎ ፡ ያዘው ።

## ጥያቄ ።

፩ ፤ ኒንያስ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ? የነገሠው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነበር ፡ ?

፪ ፤ በጠባዩ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ኑሮአል ፡ ?

፫ ፤ ሌላ ፡ ደግሞ ፡ ምን ፡ አደረገ ፡ ?

፬ ፤ ከአምስት ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ አሶር ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?

፭ ፤ ፑል ፡ ማነው ፡ ? ነቢዩ ዮናስ ፡ ወደ ፡ ነነዌ ፡ ሄዶ ፡ ንስሓ ፡ የሰበከው ፡
ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ?

፮ ፤ ሳርዳናፓሎስ ፡ ማነው ፡ ? ኑሮውስ ፡ እንዴት ፡ ኑሮአል ፡ ?

፯ ፤ አርባስስ ፡ ምንድን ፡ ነው ፡ ?

፲ ፤ ሳርዳናፓሎስ ፡ ምን ፡ አደረገ ፡ ?
የአሶራውያን ፡ መንግሥት ፡ ፍጻሜ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?
ሳርዳናፓሎስ ፡ ለሕዝቡ ፡ ሳያስብ ፡ የራሱን ፡ ደስታ ፡ ብቻ ፡ መጠበቁ ፡
ለምን ፡ ይመስልሃል ፡ ?
ንጉሥ ፡ እንኳ ፡ ቢሆን ፡ ሰነፍ ፡ ከሆነ ፡ በራሱና ፡ በሕዝቡ ፡ ላይ ፡ መከራ ፡
እንዲመጣባቸው ፡ ይህ ፡ ታሪክ ፡ አይበቃምን ፡ ?

## ምዕራፍ ፣ ፲፫ ፣ እስያ ፣ ይቀጥላል ።

### ስለ ፣ ዕብራውያን ፣ ወይም ፣ አደሁድ ፤ ስለ ፣ ዕብራውያን ፣ መጀመሪያ ፣ ነገር ።

### ያዕቆብና ፣ ልጆቹ ፣ ወደ ፣ ምስር ፣ የመውረዳቸው ፣ ታሪክ ።

፩ ፤ የዕብራውያንን ፣ ነገድ ፣ የመሠረተ ፣ የታራ ፣ ልጅ ፣ አብርሃም ፣ ነው ። የተወለደው ፣ ከጥፋት ፣ ውኃ ፣ ወዲህ ፣ ሁለት ፣ መቶ ፣ ዓመት ፣ ቈይቶ ፣ ነው ። የተወለደበት ፣ አገር ፣ ( ከላውዲዎን ፣ ) ከልዲያ ፣ ይባላል ። ይህም ፣ በአሶራውያን ፣ መንግሥት ፣ በስተደቡብ ፣ በኩል ፣ ያለው ፣ አገር ፣ ነው ።

፪ ፤ የቀሩትም ፣ የከለዳውያን ፣ ሕዝብ ፣ ጣዖት ፣ የሚያመልኩ ፣ ስለ ፣ ነበሩ ። ለፀሐይ ፤ ለጨረቃ ፤ ለከዋክብትም ፣ ይሰግዱ ፣ ነበር ። አብርሃም ፣ ግን ፣ እኛ ፣ የምናመልከውን ፣ እውነተኛውን ፣ አምላክ ፣ ያመልክ ፣ ነበር ። ቀድሞ ፣ በልጅነቱ ፣ ያደገው ፣ በከለዳውያን ፣ አገር ፣ እረኛ ፣ ሆኖ ፣ ነው ። አባቱ ፣ ከሞተ ፣ በኋላ ፣ የተወለደበትን ፣ አገር ፣ ለቆ ፣ በምዕራብ ፣ በኩል ፣ ከነዓን ፣ ወደ ፣ ተባለው ፣ አገር ፣ እንዲሄድ ፣ እግዚአብሔር ፣ አዘዘው ።

፫ ፤ ይኸውም ፣ አገር ፣ በኋላ ፣ ጳለስቲና ፣ ተባለ ። ያለውም ፣ ከዐረብ ፣ አገር ፣ ወደ ሰሜን ፣ ከሜዴቴራኒያን ፣ ባሕር ፣ ወደ ፣ ምሥራቅ ፣ በኩል ፣ ነው ። አገሩ ፣ ሀብታምና ፣ ፍሬያም ፣ ነው ። ልጆቹ ፣ በዚያ ፣ እንዲኖሩ ፣ እግዚአብሔር ፣ ለአብርሃም ፣ ተስፋ ፣ ሰጥቶታል ።

፬ ፤ አብርሃም ፣ ከሚስቱ ፣ ከሣራ ፣ ጋር ፣ ሆኖ ፣ ወዲያና ፣ ወዲህ ፣ ሲንከራተት ፣ ብዙ ፣ ዘመን ፣ አለፈ ። አያሎች ፣ ወንዶችና ፣ ሴቶች ፣ ሎሌዎችም ፣ ይከተሉት ፣ ነበር ። የከብቱም ፣ መንጋ ፣ ብዙ ፣ ነበር ። ቤትም ፣ አልነበራቸውምና ፣ መኖሪያቸውም ፣ በድንኳን ፣ ነበር ።

፭ ፤ አብርሃምና ፣ ሣራ ፣ ይስሐቅ ፣ የተባለ ፣ አንድ ፣ ልጅ ፣ ብቻ ፣ ነበራቸው ። አባቱ ፣ በጣም ፣ ይወደው ፣ ነበር ። ልጁን ፣ ለመሥዋዕት ፣ እንዲያቀርበው ፣ እግዚአብሔር ፣ ቢያዘው ፣ ለመታዘዝ ፣ ተሰናዳ ። ነገር ፣ ግን ፣ ከሰማይ ፣ መልአክ ፣ መጣና ፣ ልጁን ፣ እንዳይሠዋው ፣ ከለከለው ።

፮ ፤ የአብርሃም ፣ ሕይወት ፣ እጅግ ፣ የሚያስደንቅ ፣ ነገር ፣ መልቶበታል ። ዳሩ ፣ ግን ፣ ሁሉን ፣ በዚህ ፣ ልተርክላችሁ ፣ አልችልም ። መቶ ፣ ሰበ ፣ አምስት ፣ ዓመት ፣ ተቀምጦ ፣ በከነዓን ፣ አውራጃ ፣ ኬብሮን ፣ በተባለ ፣ አገር ፣ ሞተ ። መቃብሩም ፣ ከብዙ ፣ ዓመት ፣ በፊት ፣ ሣራ ፣ ተቀብራበት ፣ በነበረው ፣ በመክፈላ ፣ ዋሻ ፣ ነው ።

፯ ፤ አይሁድና ፣ ዐረቦች ፣ የዚህ ፣ የጥንት ፣ ፓትርያርክ ፣ ልጆች ፣ ናቸው ። መጥውንም ፣ አባታችን ፣ አብርሃም ፣ ነው ፣ ይላሉ ። እስከ ፣ ዛሬ ፣ ድረስ ፣ የአብርሃምንና ፣ የሣራን ፣ መቃብር ፣ ይህ ፣ ነው ፣ ብለው ፣ ያሳያሉ ፣ ይባላል ። ያንንም ፣ ቅዱስ ፣ ስፍራ ፣ ይሉታል ፤ ዛሬውንም ፣ አያሎች ፣ መንገደኞች ፣ ይጐበኙታል ።

አይሁድ ፡ እንዴምን ፡ ሆኑ ፡ ? ስለ ፡ ይስሐቅ ፡ ምን ፡ ትላለህ ፡ ?
ኤሳው ፡ ምን ፡ አደረገ ፡ ? ብኵርና ፡ ማለት ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?

፮ ፤ መልስ ፡ በቀድሞ ፡ ዘመን ፡ የበኵር ፡ ልጅ ፡ ከወንድሞቹ ፡ በላይ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ በወንድሞቹ ፡ ላይ ፡ ሥልጣንና ፡ ኀይል ፡ በማግኘቱ ፡ በብዙ ፡ ምክንያት ፡ ደስ ፡ ይለው ፡ ነበር ።
ኤሳው ፡ ላንድ ፡ ለጣፈጠ ፡ ምግብ ፡ ብሎ ፡ ብኵርናውን ፡ ለወንድሙ ፡ ለያዕቆብ ፡ ሸጠለት ።
ስለዚህ ፡ ያዕቆብ ፡ ለአይሁድ ፡ ሕዝብ ፡ ዋና ፡ አለቃ ፡ ሆነ ።

፯ ፤ የያዕቆብ ፡ ፲፪ ፡ ልጆች ፡ እነማናቸው ፡ ?
የያዕቆብ ፡ ፲፪ ፡ ልጆች ፡ ዘር ፡ ማን ፡ ይባላል ፡ ?

፰ ፤ በአሬት ፡ ዘፍጥረት ፡ ፴፮ ፡ ም. እንደ ፡ ተጻፈው ፡ የዮሴፍን ፡ ታሪክ ፡ ልትተርክልኝ ፡ ትችላለህን ፡ ?
የያዕቆብ ፡ ቤተ ፡ ሰቡን ፡ ጠቅሎ ፡ የተሰደደው ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ ?
ከነዓን ፡ ከምስር ፡ በየት ፡ በኩል ፡ ነው ፡ ? ምን ፡ ያህል ፡ ቀንስ ፡ ያስኬዳል ፡ ?
መልስ ፡ ከምስር ፡ እስከ ፡ ከነዓን ፡ ርቀቱ ፡ ፪፻ ፡ ማይል ፡ ይሆናል ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፩ ፡ እስያ ፡ ይቀጥላል ።

### የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ በምስር ፡ በግዞት ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ ነበሩ ።

### የዕብራውያን ፡ ሽሽትና ፡ ፈርዖን ፡ ከነሠራዊቱ ፡ እንደ ፡ ጠፋ ።

፩ ፤ እንደምታውቁት ፡ ምስር ፡ ያለው ፡ በአፍሪካ ፡ ነው ። አያሎች ፡ ከተሞችም ፡ አሉበት ። በመኻከሉ ፡ ናይል ፡ የተባለ ፡ ስመ ፡ ጥሩ ፡ ወንዝ ፡ ይሮጥበታል ። ዛሬ ፡ በገሩ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ሕዝብ ፡ ብዛቱ ፡ በዮሴፍ ፡ ጊዜ ፡ ከነበረው ፡ ሕዝብ ፡ ያንሳል ። የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ሕዝቡ ፡ ብዙ ፡ ነበሩ ። በዓለም ፡ ላይ ፡ ከሚገኙ ፡ ሕዝቦች ፡ (ነገዶች ፡) ይልቅ ፡ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ምስሮች ፡ በትምህርትና ፡ በሥልጣኔ ፡ እጅግ ፡ ከፍ ፡ ያሉ ፡ ነበሩ ። የጥንት ፡ ሰዎች ፡ የሠሩዋቸው ፡ እጅግ ፡ የሚያምሩት ፡ የቤተ ፡ መንግሥትና ፡ የከተሞች ፡ ፍራሾች ፡ በምስር ፡ ይገኛሉ ።

፪ ፤ ስለ ፡ ዕብራውያን ፡ ልንገራችሁ ፤ ደጉ ፡ ፈርዖን ፡ የምስር ፡ ንጉሥና ፡ ዮሴፍ ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ ዕብራውያንን ፡ የሚጠላ ፡ እጅግም ፡ ግፍ ፡ ያደረገባቸው ፡ ሌላ ፡ ንጉሥ ፡ በዙፋን ፡ ላይ ፡ ተቀመጠ ።

፫ ፤ ዕብራውያንን ፡ ምስሮች ፡ እንደ ባሪያ ፡ አድርገው ፡ ገዙዋቸው ፤ እጅግ ፡ ጠንካራ ፡ የሆነውን ፡ ሥራ ፡ የሚሠሩ ፡ ዕብራውያን ፡ ነበሩ ። ያን ፡ የተከመረ ፡ የድንጋይ ፡ ክምር ፡ ዛሬ ፡ ፒራሚድ ፡ የሚሉትን ፡ የሠሩ ፡ ዕብራውያን ፡ ናቸው ፡ እያሉ ፡

